# የግንቦት ቅልበሳ

## ምን መዘዝ? ምን አፀፋ?

### ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የቀረበ የመወያያ ሰነድ

*መግቢያ -*

ዛሬ ሶስተኛ አመቱን በምናከብረው የግንቦት 97 ታሪካዊ ምርጫ የኢህአዴግ መሪዎች በገጠርም በከተማም ከተሸነፉ በኋላ በሃገራችን በመትከል ላይ ያሉትን የሽብር አገዛዝ ብዙ ዜጎች ከየካቲቱ አብዮት ቅልበሳ ጋር ተያይዞ በህዝባችን ላይ ከወረደው የቀይ ሽብር መአትና ዙሪያ ገጠም ቀውስ ጋር ሲያነፃፅሩ ይስተዋላሉ። እውነታቸውን ነው። የግንቦትም ሆነ የየካቲት ቅልበሳ መነሾዎች እንደ ውሃ ጠብታ የሚመሳሰሉ ናቸው። የግንቦት ማግስቱ ቀውስ ዋና ምክንያት የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ለአስራ አራት አመታት ስለ ዴሞክራሲ፤ ስለ ነፃ ፕሬስ፤ ስለ መደራጀት መብት፤ ስለነፃ ምርጫና ከዚህ ሁሉ አልፈው ተርፈው ስለ "ጠንካራ ተቃዋሚ" ማግት ላንቃቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ የሆነ ያልሆነውን ከለፈፉ በኋላ የዚህን ሁሉ "መዘዝ" በፀጋ መቀበል ስላልቻሉ እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል። የየካቲቱ አብዮት ማግስት ቀውስም ከዚህ የተለየ መነሾ አልነበረውም። ሃገራችን እስከዛሬ አወራርዳ ያልጨረሰችው የጥፋት አዙሪት ውስጥ የገባችው ያኔ የደርግ መሪዎች ስለ መሬት ለአራሹ፣ ስለ ህዝብ የስልጣን ባለቤትነትና በተለይም ስለ ገበሬው "ራሱን በራሱ የማስተዳደር" መብት ወዘተ ያወጧቸውን አዋጆችና በወቅቱ የመኢሶን ልሳን "የሰፊው ህዝብ ድምፅ" (ቁ.69) እንዳስቀመጠው "በየአደባባዩ፣ በየሴሚናሩና በየአለበት ግራ እጃቸው ከትከሻቸው ተነቅሎ እስኪሄድ ድረስ ከህዝቡ ጋር ያስተጋቧቸውን" አቋሞች የፖለቲካና የኢኮኖሚ "መዘዞች" መቀበል ስላቃታቸው ነበር።

ትላንት የደርግ መሪዎች ታላቁ የመሬት አዋጅ ታላቅ አለመግባባት የነበረ ይመስል "መሬት ለአራሹ " ብለው ገበሬው ይህንን አዋጅ እውን ለማድረግ ከባድ መስዋእትነት የጠየቀ ተጋድሎ አካሂዶ ፊውዳሊዝምን ከደመሰሰና በወቅቱ ዴቪድ ኦታዌ የተባለ ጋዜጠኛ "የኢትዮጵያ ተአምር" ብሎ በጠራው ክስተት እዛው በዛው ለአብዮቱ እየተዋደቀ ምርቱን አሳድጎ፣ ጠግቦ መብላትና የአዲስ ኑሮ ተቋማቶቹን መገንባት ከጀመረ በኋላ "ምርት ግን ለመንግስት!" በማለት እንደ ግንቦት ገና ከምሰቡ ሳይሆን ህዝባችን እጁ አስገብቷቸው የነበሩትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ድሎች በአመፅ ቀምተውታል። በፖለቲካውም መስክ ህዝባችን በተለይም ገበሬዎች "መሪዎቻችሁን በየደረጃው እየመረጣችሁ ራሳችሁን በራሳችሁ አስተዳድሩ" ተብለው በየካቲት 67 አ.ም. ከመሬቱ አዋጅ ጋር ታውጆ የነበረው የመደራጀት መብት ውሱንነት ታይቶ በታህሳስ ወር 1968 አ.ም. "የገበሬ ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ" ወጥቶ አሁንም ከባድ መስዋእትነት ተከፍሎባቸው በገበሬው ተመርጠው፣ ገበሬው የኔ የሚላቸውና በእርግጥም ለገበሬው የሚያገለግሉ በወቅቱ ሃገራችን ይኖር የነበረ ዣክ ቢሮ የተባለ ተመራማሪ "የገጠር መንግስታት" ብሎ የጠራቸውን የራስ አስተዳደር ተቋማት ከመሰረቱ በኋላ እነዚህን ማህበራት በደም ባህር አጥለቅልቀውና አፈራርሰው ተጠሪነታቸው ለህዝብ ሳይሆን ለደርግ በሆኑ የመንግስት ካድሬዎች እንዲተኩ አድርገዋል። ዛሬ ደግሞ የኢህአዴግ መሪዎች "ነፃ ምርጫ ነው" ካሉ በኋላ "ነገር ግን እኛ ካልተመረጥን አይሰራም!" ብለው ህዝባችንን ለዚህ ድል ያበቁትን ህጋዊ ተቋማት እያፈራረሱ፣ የነፃውን ፕሬስ ደብዛ እያጠፉ፣ ከዝቅተኛ ዝቅተኛ የሚባሉ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እያወደሙ፣ ይህንን ሁሉ ላሻፈረኝ ባለ ህብረተሰብ ላይ በሽብር ተሰማርተው እናያቸዋለን።

የካቲትና ግንቦት በዚህ መልክ የሚመሳሰሉት በመነሻቸው ብቻ አይደለም። መዘዛቸውም የተለያየ ሊሆን አይችልም። በየካቲት ቅልበሳ በ1970 አ.ም. በቀይ ሽብርና በአፈና ውርጅብኝ አንድ ታጋይ ትውልድ ተሰውቷል። ሆኖም ከዚህ መአት የተረፈው ሃይል ከሃገር ፍቅሩም ሆነ ለዚች ሃገርና ህዝብ ለመሰዋት ካለው ቁርጠኝነት ምንም ሳይጎድለው በተለያዩ ውስጣዊና አለም አቀፋዊ፣ ታሪካዊና ጊዜያዊ ምክንያቶች ለሁኔታው የሚመጥን አፀፋ ሰጥቶ ቅልበሳውን መቀልበስ ባለመቻሉ የሃገራችን ፈተና በዚህ አላበቃም። የየካቲትን ቅልበሳ መዘዞች ዘወር ብለን ስንቃኝ የአፈናው ውርጅብኝ መጀመሪያ ላይ በተወሰኑ ተቃዋሚዎች ላይ ያተኮረ ቢመስልም ቀስ በቀስ በጠቅላላው መሬትና ምርት ላራሹ ይሁኑ፣

ህዝባዊ ዴሞክሲያዊ ማህበራት ያብቡ እያለ ደርግም ራሱ ሲያስተጋባቸው ለነበሩትና በውሳኔም በአዋጅም ላፀደቃቸው አላማዎች ለተዋደቀው በከተሞች በተለይም ደግሞ በገጠር በመቶ ሽህ ለሚቆጠር ዜጋ የተረፈ መአት እንደነበረ እንመለከታለን። በዚህ መልክ ግንባር ቀደሙ ሃይል ከተመታ በኋላ የአፈናው ውርጅብኝ አይን በሚስብ መልኩ ጋብ ቢልም በቀጠሉት አመታት የደርግ መሪዎች ባሻቸውና እንዳመቻቸው በሃገራችን ላይ በተከሏቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ሳቢያ ሃገራችን የሰማይ ስባሪ ለሚያክሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የፖለቲካ፤ የሞራልና ስነልቡናዊ ቀውሶች ተዳርጋለች።

የግንቦቱ ቅልበሳ ገና በሂደት ላይ ነው። ነገር ግን መኢሶን ከወዲሁ በእርግጠኛነት ማለት የሚችለውና ለሃገራችን ዴሞክራቶች እንደ ማስጠንቀቂያ የሚሰነዝረው አንድ ቁም ነገር አለ። "ሁላችንም ለግንቦት ድሎች!" ብለን ምስኪንና ዘግናኝ የድርጅት ስሌቶችን ወዲያ አሽቀንጥረን ጥለን በጋራ ካልተንቀሳቀስንና ቅልበሳውን ከህዝባችን ጋር ሆነን በጊዜ ካልቀለበስነው የሃገራችን ፈተና አሁን በሚታየው የአፈና ውርጅብኝ የሚቆም አይሆንም። የኢህአዴግ መሪዎች በሽብር ሊያንበረክኩት በሚሞክሩት ህብረተሰብ የሚተክሏቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በየካቲት ማግስት እንዳየነው በሚልዮን ለሚቆሩ ወገኖቻችን ህልውና ብሎም ለሃገራችን ሰላምና አንድነት ለማሰብ እንኳን የሚቀፉ መዘዞች ይኖሩታል።

ይህንን አስከፊ አደጋ ለመቋቋም በእኛ እምነት መወሰድ አለባቸው የምንላቸውን የአፀፋ እርምጃዎች ውይይት እንዲደረግባቸው ከመጠቆማችን በፊት መጀመሪያ ስለ ግንቦት ድሎችና ስለቅልበሳው ምንነት ያለንን አስተሳሰብ በአጭሩ አስቀምጠን ከዚያም ይህ ቅልበሳ ከቀጠለ ከየካቲትም ከተቀሰመው ትምህርት ሆነ ዛሬ እያየን ካለነው ተነስተን በመጭው ጊዜ ስለሚጠብቁን ሶስት የተያያዙ የቅልበሳ መዘዞች በአጭር በአጭሩ ለማስቀመጥ እንሞክራለን።

## ክፍል አንድ - ምን ቅልበሳና ምን መዘዝ?

የተያዘው ቅልበሳ አላማና ኢላማ እንዲገባን መጀመሪያ ግንቦት ምን ድል ነበር? እነዚህስ ድሎች እንዴት ተገኙ የሚሉትን ጥያቄዎች ባጭሩም ቢሆን ለመመለስ መሞከር ያስፈልጋል። በኛ እምነት ግንቦት ተራ ምርጫ ሳይሆን በምርጫ ሰቢያ የተካሄደ ህዝባዊ አብዮት ነበር። ድሉም ተራ የድምፅ ብልጫ ድል አልነበረም። በአመፅ እየታጀበ ከሚከናወንና ህብረተሰባችንን ለዘመናት ሲያደማ ከቆየው ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰላማዊ ዘዴና በምርጫ ካርድ ህዝባችን የመንግስት ለውጥ አደረገ። ህዝብን ከህዝብ እያናከሰ ለመግዛት ከሚሞክረው ስርአት አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አንድ ሰው ቆሞ በእኩልነትና በወንድማማችነት ለምትመሰረት አንዲት ኢትዮጵያ ያለውን ፍላጎት አሳየ። ከታሪካችን ከተወረሰው የአሸናፊ ተሸናፊ አዙሪት ተላቆ ለብሄራዊ እርቅ ፖለቲካ መቆሙን በግልፅ አስታወቀ። ይህንን ፀረ ህዝብ ህገ መንግስት ሽሮ ለዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት መቆሙን አስመሰከረ። ግንቦት የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ልብና እኛን ባኮራ፣ አለምን ባስደነቀ፣ የኢህአዴግ መሪዎችን ብርክ ባስያዘ ወኔ የተንቀሳቀሰበትና ዴሞክራሲ በአፋኝ አገዛዝ ላይ፤ የሰላማዊ ለውጥ ሃሳብ በአመፅ ፖለቲካ ላይ፤ የህዝቦች ወንድማማችነት እሴት በከፋፍለህና አናክሰህ ግዛ ርኩስ ፖሊሲ ላይ ድል የተጎናፀፉበት ሂደት ነበር።

ይህ በፖለቲካውና በስነልቡናው መስክ የተገኘው ውጤት የግንቦት ድሎች አንዱ ገፅታ ብቻ ነው። በግንቦት ዘመቻ ወቅት በኢኮኖሚና በማህበራዊ ፖሊሲዎች ዙሪያ በመንግስትና በተቃዋሚዎች መሃከል በህዝብ ፊት ሰፋፊ ክርክሮች ተካሂደዋል። ይህም በመሆኑ ግንቦት በሃገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባችን ርሃብ፣ በሽታ፣ ድህነትና የእርዛት ኑሮ ለአርባ ቀን እድል የሚተው ነገር ሳይሆን የአጥፊና የአልሚ ፖሊሲዎች ጥያቄ እንደሆነ ግንዛቤ እንዲያገኝና ይሻለኛል ለሚለው አማራጭ ድምፁን ለመስጠት የተንቀሳቀሰበት ታሪካዊ ሂደት ነበር። ዛሬ እኛ በአፈናውና በሽብሩ እየተዋከብን በምንገኝበት የተከላካይነት ሁኔታ ድሉን በድምፅ ብልጫ ድል፣ ቅልበሳውን ደግሞ እጅግ ጠባብ በሆነው "በድምፅ ስርቆሽ" ገፅታው ወስነን ላይ ታች ስንል ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር ስለተያዘው ወሳኝ ፍልሚያ ይዘትና ምንነት በቂ ግንዛቤ ያለ አይመስልም። የቅልበሳው አላማ በአንድ በኩል ህዝባችንን ለዚህ ድል ያበቁትን ተቋማት፣ የፖለቲካ ጥራትና ስነልቡናዊ ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርጎ የማውደም በሌላ በኩል በሃገርና በህዝብ ኪሳራ ለጥቂቶች የተበጁትን አ

ጥሬ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎችን በመቀጠል ሃገራችንን የጥቂቶች ገነት የሚልዮኖች የሰቆቃ ምድር የማድረግ አላማ አለው።

ተቋማትን የማፈራረስ የሚለውን የቅልበሳውን የመጀመሪያ አላማ እንመልከት። የየካቲትን ቅልበሳ አካሄድ ስን መለከት መጀመሪያ በህብረ ብሄር ደረጃ ተደራጅተው የደርግን አገዛዝ ሊተኩ በሚችሉ ድርጅቶች - ማለትም በኢህአ ፓ፣ መኢሶንና ኢዲዩ - እና ደጋፊዎቻቸው ላይ አነጣጥሮ በሃገር ደረጃ የአማራጭ ክፍተት የመፍጠር አላማ ነበረው። ከዚህ በተጓዳኝ የታየው ደግሞ በከተማ በተለይ ደግሞ በገጠር እዛው በዛው የአብዮቱ ውጤትም አራማጅም የሆኑትን ህዝባዊና አብዮታዊ ተቋማትን አፈራርሶ የሚፈጠረውን ክፍተት ለደርግ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት የመተካት አካሄድ ነበር። ዛሬም የተያዘውን የቅልበሳ ጥረት ከዚህ የተለየ አላማ የለውም።

ላለፉት አስርት አመታት ህብረተሰባችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዳይሸጋገር አንቆ ይዞት የነበረው በተቋ ማት፤ በፖለቲካና ስነልቡናዊ መስክ ይታይ የነበረው "የሽግግር ክፍተት" ነበር። ግንቦት 97 ይህ ክፍተት በመጠኑም ቢ ሆን ተደፍኖ ህብረተሰባችን በሰላማዊ ዘዴ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ብቃት እንዳለው ያሳየበት ሂ ደት ነበር። በግንቦት ዋዜማ ሃገራችን በተቋማትም ሆነ በአስተሳሰብ ደረጃ ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በታሪካችን ከዚህ በ ፊት ባልታየ ሁኔታ ዝግጁ ነበረች። በዚህ ጉዳይ መኢሶን በ1964 ኢ.ም. "ተሸጋጋሪው ማነው? አሸጋጋሪውስ?" ባሳተመው "የሰፊው ህዝብ ድምፅ" ልዩ እትም በሁለት የሽግግር ቁልፍ ጥያቄዎች ዙሪያ አስፍሯቸው የነበሩትን ነጥቦች እንመል ከት፤

" መጀመሪያውና አዲስና ለሰላማዊ ሽግግር አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል የምንለው የታሪክ አጋጣሚ በቀደሙት በሁ ለቱ የሽግግር ወቅቶችም ሆነ በአጠቃላይ በታሪካችን ያልነበሩ አዳዲሲ ተቋማትን መከሰት የሚመለከተው ገፅታ ነው። ዛሬ በውጭ አገር በይፋ በውስጥ ደግሞ በህቡእ መዋቅራቸውን ዘርግተው ከሚንቀሳቀሱት በርካተር ተቃዋሚ የፖለቲ ካ ድርጅቶች በተጨማሪ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ በሀርገሪቱ ውስጥ በህግ ታውቀው የሚንቀሳቀሱና በሚልዮን የሚ ቆጠር ህዝብ ከጎናቸው ሊያሰልፉ የሚችሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። በውጭ አገሮች በሃገር ጉዳይ ዙሪያ ትግላቸውን- በቀጥታ ከፖለቲካ ሳያያይዙ ለሃገርና ለወገን የሚታገሉ የሲቪክ ማህበራት እንደ አሸን እየፈሉ ባሉበት ወ ቅት እንደዚሁ ለመጀመሪያ ጊዜ የሲቪክ ማህበራት ባህል (ኤንጂኦ ከልቸር) በሀርገራችን ምድር ስር እየሰደደ ነው። በ ደርዘን የሚቆጠሩ ማህበራት ከመንግስት ውጭና አንዳንዴም መንግስትን እየተቃወሙ ( በዚህም የተነሳ መሪዎቻቸው ለ እስራት፣ ለግድያ፣ ለስደትና ለእንግልት እየተጋለጡ) በይፋና በህጋዊ ዘዴ የሚንቀሳቀሱበትና ከፖለቲካ ውጭ ተደራጅ ቶ ለሃገር፣ ለወገን፣ ለመብት፣ ለሙያና ለህጋዊ ጥቅም፣ ለባህላዊ ህል-ውናና ለመሳሰሉት አላማዎች የመንቀሳቀስ ልምድ እየዳበረ በመሄዱ በሃገሪቱ የዴሞክራሲ መስፈን ሂደት ትልቅ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ማህበራትና ለፒሎች ስብስቦች ተበራክተዋል። በየእለቱ ለነፃነቱና ለህል-ውናው እየደማና እየተዋከበም ቢሆን ዛሬ በሃገራችን በቀደሙት የሽግግር ወቅ ቶች ያልነበረ ከመንግስት ቁጥጥር ነፃ የሆነ ፕሬስ አለ። ገና ሙሉ በሙሉ ያልተሰበረውን የመንግስት ሞኖፖል ለመስበ ር ከውጭ አገር ጥረት የሚያደርጉ ራድዮ ጣቢያዎች እየተበራከቱ መጥተዋል" ካለ በኋላ መኢሶን በዚሁ ሰነዱ አያይዞ ከዚህ ሁሉ በጎ ለውጥ ጋር በፖለቲካ አስተሳሰብ መስክ ስለተደረገው ለውጥና ህብረተሰባችን ስለደረሰበት አጠቃላይ ስ ምምነት ወይም "ኮንሰንሰስ" ሲተች፣

" ከነዚህ ሁሉ ክስተቶች ጋር ተያይዞና ከነሱም ጋር እየተጋገዘ ያደገ የሃገራችንን የወደፊት አጠቃላይ እርምጃ በተመለከተ ወደ መድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መሸጋገር አለብን የሚል አጠቃላይ ስምምነት አለ። እርግጥ ዛ ሬም ቢሆን በዚህ መሰረታዊ የአቅጣጫ ጥያቄ ላይ በአንድ በኩል በተቃዋሚ ሃይሎችና በጠቅላላው በህብረተሰቡ በሌላ በኩል ደግሞ ስልጣን ላይ በሚተራመሱት አንጃዎችመሃከል መሰረታዊ የሚባሉ ልዩነቶች አሉ። ነገር ግን ይህ ጥቂት ፀረ ዴሞክራሲ የሆኑ ሃይሎች ከህ-ብረተሰቡ አፈንግጠው የሚያራምዱት ፀረ ዴሞክራሲያዊ አቋም መሰረታዊውን በሃገሪ ቱና በህ-ብረተሰባችን ውስጥ ያለውን እውነታ አይቀይ-ረውም። ዛሬ ከነዚህ ጥቂቶች በስተቀር በሃገሪቱ በመንቀሳቀስ ላ ይ ያሉ ሃይሎች በሙሉ የሰው ልጅ መብቶች ያለአንዳች መሸራረፍ ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት፣ የህ-ግ የበላይነት ሙ ሉ በሙሉ የሚረጋገጥበት፣ የህዝቦቻች-ን እኩልነትና ወንድማማችነት የሚረጋገጡበት የመድበለ ፓርቲ ስርአት ይጠይ ቃሉ።"

እነዚህ መስመሮች ከተፃፉ ሶስት አመት በኋላ የተካሄደው የግንቦት 97 ምርጫ የዚህን ትንተና ትክክለኝነት አረጋግጦ ህብረተሰባችን በህጋዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ዘዴ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ብቃቱም ፍላጎቱም እንዳለው አሳይቷል። የግንቦትን ቅልበሳ አሳሳቢ የሚያደርገው በእነዚህ ባለፉት አስራ አራት አመታት ቀስ በቀስ ታጋይ ዜጎች እየሞቱ፣ እየታሰሩ፣ እየተሰደዱ በገነቧቸውና የወያኔ/ኢህአዴግን መሪዎች ለሽንፈት በዳረጓቸው ታሪካዊና ዴሞክራሲያዊ ግኝቶች ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ነው። ኢዴሃህ ”አንድነት ለነፃነትና ለዴሞክራሲ” የተባለው ድርጅት ለተቋቋመበት የዩትሬክት (ሆላንድ) ስብሰባ ባስተላለፈው መልእክት፣

”ዛሬ በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ትግል ማንም የፖለቲካ ሃይልም ሆነ ስብስብ የሚያወጣው ስትራቴጂ በአጥፊነትም ሆነ በአልሚነት የሚመዘነው ከነዚህ ድሎች አንፃር በሚወስደው አቋም ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ህልማቸው የህዝብ ድምፅ ሰርቀው ለሌላ አምስት አመት በስልጣን ላይ ለመቆየት ብቻ የሚጥር ህልም አይደለም። ዛሬ በአይናችን ስር እየተካሄደ ካለው ዘግናኝ የሽብር ውርጅብኝ ባሻገር ሙከራቸው ህብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ብቁ ያደረጉትን በመስዋእትነት የተገነቡ እነዚህን ተቋማት በማፈራረስና በህዝባችን ስነ ልቡና የሰረፁትን በጎ ያስተሳሰብ ለውጦች በማውደም የዛሬ ሃያም ሰላሳም አመት የነበረውን ”የሽግግር ክፍተት” መልሶ እውን ለማድረግ የሚጥር መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ ነው።” የተያዘውን ቅልበሳ ርኩስ ተልእኮ በሚገባ ተችቶበታል።

ከዚህ ተቋማትንና በጎ ስነልቡናዊ ግኝቶች ከማውደም አላማ በተጓዳኝ ቅልበሳው ከፍ ተብሎ እንደተጠቀመው ግንቦት ላይ ህዝባችን ድምፅ የሰጠባቸውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች ረግጦ የአሸነፍን ባዮቹን የጥፋት ጉዞ የመቀጠል አላማ አለው። ነፃ ምርጫ ብቻውን የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም። ህብረታችንም ሆነ ቅንጅት ምርጫ ሲገቡ ህዝባችንን የተሻለ ቀን እናመጣልሃለን ምረጠን ብለው ዘመቻ አካሂደዋል። በምርጫው ዘመቻ ወቅት የኢህአዴግን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በአደገኛነትና በአጥፊነት ፈርጀው እነዚህ ፖሊሲዎች በአስደንጋጭ ሁኔታ ”መመለሻ ወደሌለው ደረጃ” እየተሸጋገሩ ነው ብለው፣ ለነዚህ ፖሊሲዎች አማራጭ ፕሮግራሞች አንግበው ታግለዋል።

ህዝባችን በግንቦት ምርጫ በድል አድራጊነት ወጣ ሲባል ህብረቱ ብቻ ሳይሆን ቅንጅቱም ለነዚህና ለሌሎች ቁልፍ የህዝባችንን ህልውና የሚመለከቱ ጉዳዮች በመፍትሄነት የቀረቧቸው አማራጮች ተቀባይነት አገኙ ማለት ነበር። ኢህአዴግ ምርጫ አሸነፍኩ ብሎ በማንአህሎኝነት አገዛዙን ሲቀጠል ደግሞ ህዝቡ ይበጀኛል ብሎ ከተቀበላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ይልቅ በእነዚህ ለድርጅቱ መሪዎችና ለጥቂት ተባባሪዎቻቸው ብቻ ተሰልተው በስራ ላይ የሚውሉ ፀረ ህዝብና አገር አውዳሚ ፖሊሲዎች የመቀጠል አላማ እንዳለው ግልፅ ነው።

ህብረተሰባችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር በተያያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ የቅልበሳውን አላማ በዚህ ፖለቲካዊ፣ ስነልቡናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ በሆነ ዘርፈ ብዙ ገፅታው መረዳት ለቀጣዩ ትግልም ይዘት ወሳኝ ነው እንላለን። በዚህ ጉዳይ መጀመሪያ የቅልበሳውን መዘዞች በተመለከተ ያለንበትን ሁኔታ ከገለፅን በኋላ መስጠት ስላለብን አፀፋ በምንተነትንበት ክፍል በሰፊው እንመለስበታለን። እዚህ ላይ ግን ቆም ብለን በተቃዋሚው ጎራ የቅልበሳውን እውንነት፣ አሳሳቢነትና ቀጣይነት የሚክዱ አንዳንድ ወገኖች በተሰማሩበት ትጥቅ አስፈቺ አካሄድ አንዳንድ ነጥቦችን ለማስቀመጥ እንሞክር።

ከአመት በፊት ”አስፍቶ ማየት፣ አርቆ ማየት” በሚል ርእስ ከኢዴሃህ በተሰጠ መግለጫ በትክክል እንደተጠቀመው እርግጥ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር የተሟላ ዴሞክራሲ ኖሮ አያውቅም። ነገር ግን የኢህአዴግ መሪዎች ካሉበት የኪሳራ ደረጃ አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ ” የተሟላ ዴሞክራሲ ” ሳያስፈልገው በቅድመ ግንቦቱ ወቅት በነበረችው የዴሞክራሲ ፍንጭ ተጠቅሞ በፀረ ህዝቦቹ ላይ የማያወላዳ ድል ለመጎናፀፍ በቅቷል። ከዚህ መቅሰም ያለብን ትምህርት በጣም ግልፅ ይመስለናል። ገና በእንጭጩ የነበረው የዴሞክራሲ ሂደት ምን ያህል ኪሳራ እንዳደረሰባቸው ተገንዝበው በለየለት ሽብር ለመሰማራት የተገደዱት የኢህአዴግ መሪዎች ከእንግዲህ በህዝብ ትግል ከጥፋት ሂደታቸው ለማፈግፈግ ከመገደዳቸው በፊት እንደ ዳኝነት ነፃነት፤ የህግ የበላይነት፤ ነፃ ምርጫ፤ ተጠያቂነት ወዘተ የመሳሰሉት ከባድ ከባድ እሴቶች ቀርቶ ቅድመ ግንቦት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች እንኳን መልሰው እውን ይሆናሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም።

በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ተቃዋሚ ተብየዎች አካባቢ ይህንን ሃቅ ከመቀበል ይልቅ ስለ ድርድር፣ ስለ ብሄራዊ
እርቅና ስለ ቀጣይ ምርጫ እየተለፈፈ ''ቅልበሳውንና አስከፊ መዘዞቹን ህዝባችንን ይዞ መታገል'' የሚለውን አቋም እን
ደ ''አክራሪዎች'' ጥያቄ አድርጎ የማቅረብ ዝንባሌ ይታያል። እነዚህ ወገኖች ልክ እኛም እንደምንለው ከቅድመ ግንቦቱ
ወቅት አንፃር ዛሬ በዴሞክራሲ ጉዳይ እጅግ ወደ ኋላ መሄዳችንንና እየተተከለ ያለውን የአፈና አገዛዝ እውንነት ለመ
ካድ አይችሉም። የምንለያየው ለሁለት ጥያቄዎች በምንሰጠው መልሶች ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ ይህ ልክ ያጣው
የአፈና ሂደት ቀጣይነት ያለው ቅልበሳ አካል ነው ወይስ ''አዘቦታዊ'' ሊባል የሚችል ከአንድ ፀረ ዴሞክራሲ ሃይል የሚ
ጠበቅና ቀስ በቀስ ''ቀውጢው ጊዜ ሲያልፍ'' የሚረግብ ክስተት? የሚለው ጥያቄ ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ ነገ የአፈ
ናው ውርጅብኝ ''አይን በሚሰብ'' መልኩ ረገብ ስላለ ብቻ ቅልበሳው አከተመ ማለት ነው? ወይስ ሃገራችን እንደ የካቲ
ት ቅልበሳ ማግስት ዙሪያ ገጠም የቀውሶች አዙሪት ውስጥ የመግባቷ አደጋ አለ? የሚለው ጥያቄ ነው። ለእነዚህ ሁለት
ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ በሃገራችን ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ተጋድሎ እጣ ፈንታ የሚወስን ይሆናል። በኛ በኩ
ል ያለን መልስ አጭርና ግልፅ ነው። አንደኛ የተያዘው የለየለት የቅልበሳ ሂደት ነው እንላለን። ሁለተኛ ይህንን ቅልበሳ
በጋራ ትግል ተረባርበን ካላቆምነው የግንቦትን ምእራፍ እኛ ብንዘጋው የኢህአዴግ ፀረ ህዝቦች የቅልበሳውን ሂደት በ
መልካም ፈቃዳቸው የሚዘጉት ፋይል ስላልሆነ በመጭው ጊዜ ሃገራችን የከባድ ቀውሶች አዙሪት ውስጥ የመግባቷ አደ
ጋ አለ።

'' የቅልበሳ አካል አይደለም፣ የተያዘው አፈናና መብት ረገጣ እስካሁን ከታየው የከፋ ቢሆንም የግንቦት ማግስ
ት ውጥረት ሲረግብ ነገሮች ቢያንስ ወደ ቅድመ ግንቦቱ ሁኔታ ሊመለሱ ይችላሉ'' የሚሉ ወገኖች ''ለመከራከር'' የሚ
ሞክሩት በሌላና የወያኔ/ኢህአዴግና የባእዳንን ጭንቀት ለማስተናገድ በሚሞክር በአልሆነ አቅጣጫ ነው። ይኸውም ''ዛ
ሬ የተከሰተው ችግር 'ጊዜያዊ' የሆነ፤ የኢህአዴግ መሪዎች 'ያልጠበቁትና ያልተዘጋጁበት' ሽንፈት ስለደረሰባቸው 'ከመ
ደናገጥ' የመጣ ችግር ነው። በመሆኑም ህዝባዊ ትግሉን ማፋፋም ድንጋጤያቸውን ይበልጥ አሳድጎ ብርክ በያዘው ጉልበ
ት ግራና ቀኝ እየተማቱ ሃገሪቱን ወደ ጥፋት ይዘው የሚነጉዱበት ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል'' የሚል ክርክር ነው። የነ
ዚህ ወገኖቻችን ክርክር ዞሮ ዞሮ ደግሞ ዴሞክራሲ ቀስ በቀስ ''በሂደት የሚገነባ'' እሴት መሆኑን በመገንዘብ በረጋ መን
ፈስና በሰከነ ተቃውሞ፣ ''በጥበብና በጥንቃቄ'' በሚካሄድ የዲፕሎማሲና ሌላ የፖለቲካ ትግል መስመር የሳተውን የዴ
ሞክራታይዜሽን ሂደት መልሶ በእግሩ ማቆም ይቻላል የሚል ህልም ላይ የሚመረኮዝ ክርክር ነው። ዞሮ ዞሮ ይህ ሁሉ
የሚያመራው በትርምስ ላይ ትርምስ ላለመጨመር፤ በኢህአዴግ መሪዎች ሰፈር ያለውን መደናገጥ ላለማገዝ ወዘተ የዚ
ህ መደናገጥ ምንጭ የሆነውን የህዝባዊ ትግል ምእራፍ 'ለጊዜው' እንዝጋው ወደሚል መደምደሚያ እንደሆነ ግልፅ ነው
። መስከረም 98 መጨረሻ ተጠርቶ የነበረው የቤት መዋል አድማ እንዲሰረዝ ተደርጎ ዛሬ ላለንበት ውጥንቅጡ የወጣ
ሁኔታ የበቃነው በእንዲህ አይነቱ አደገኛ ስሌት ምክንያት እንደሆነ ጨርሶ መረሳት የለበትም።

በዚሁ 'በነካ እጃቸው' እነዚህ ወገኖች ''ቅልበሳ እየተካሄደ ነው! ይህንን ሂደት ህዝባችንን ይዘንና በጋራ ታግለ
ን ካልቀለበስነው አስከፊ መዘዝ ይኖረዋል!' ብለን የህዝቡ ትግል እንዲቀጥልና እንዲፋፋም ጥሪ የምናደርገውን ዴሞክ
ራቶች የሃገራችንን ሰላም አደጋ ላይ ለመጣል ላይ ታች እንደሚሉ ሃላፊነት የጎደላቸው የአመፅና የትርምስ አራማጅ ሃ
ይሎች አርገው ፈርጀው ራሳቸውን ደግሞ 'ሃላፊነት የተላበሱ' የሰላምና የመረጋጋት ሃይሎች አድርገው ለማቅረብ ይሞ
ክራሉ። ነገሩ ግን የተገላቢጦሽ ነው። ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ ቅልበሳው ከቀጠለ አይቀሬ ከሚሆነ
ው ዙሪያ ገጠም ቀውስ አንፃር ሲታይ በሃገራችንና በህዝባችን ላይ ይህ ነው የማይባል አመፅና ፈተና የሚጋብዘውና ይህ
ንን ሰማእት ህዝባችንን እጅ እግር ለሌላቸው ቀውሶችና ትርምሶች የሚዳርገው አቋም ''ለሰላምና መረጋጋት ስንል'' የግ
ንቦትን የህዝባዊ ትግል ምእራፍ በዚሁ እንዝጋው የሚለው አካሄድ ነው።

በዚህ መልክ የቅልበሳውን እውንነትና አሳሳቢነት የሚክዱት ወገኖች አካሄድ ተራ ሎጂክ እንኳን የሚከተል አ
ይደለም። አፈናው እየሰፋና እየከፋ ይሄዳል፤ ሃገራችን ውጥንቅጡ የወጣ የቀውስ አዙሪት ውስጥ ትገባለች ስንል ይህን
ን ማስጠንቀቂያ እንደ ተራ 'የተቃዋሚ ልፈፋ አርገው ሲወስዱ እነዚህ ዜጎች ለአንድ መሰረታዊ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ
መስጠት አለባቸው። ከፍ ብለን በጠቀስነው የኢዴሃህ መግለጫ እንደተቀመጠው ህዝባችን በአፈናና በሽብር ብቻ ሳይ
ሆን በአመራር መዝረክረክና ክፍተት ግራ ተጋብቶ የትግል ትጥቁን ከፈታ በኋላ የኢህአዴግ መሪዎች ምን ገዷቸውና

ማን አስገድዷቸው ነው የቅልበሳውን ፋይል የሚዘጉት? በበኩላችን አደገኛ የሆነ የህልም አለም ውስጥ ስለማንኖር ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ አጭርና ግልፅ ነው። ማንም አያቆማቸውም። ይቀጥሉበታል።

ከዚህም አልፎ መሄድ ይቻላል። ቅልበሳውን ለመቀልበስ የጋራና የተሳካ ትግል ካልተደረገ የሚከተለው ችግር በአሉበት የመርገጥ ችግር ብቻ አይሆንም። እርግጥ የካቲት ላይ እንደታየው እንደ ቀይ ሽብር ማግስት የአፈናው ውርጅብኝ አይን በሚስብ ገፅታው ረገብ ሊል ይችላል። ነገር ግን ይህ የቅልበሳውን መደርጀትና መደራጀት ብሎም የሃገራችንን ወደባሰ የቀውስ አዙሪት መግባት የሚያመለክት እንጂ ለህብረተሰባችን የእፎይታ ዘመን የሚያበስር ሂደት አይሆንም። ከዚህ ተነስተን ነው ስለቅልበሳው ቀጣይ መዘዞች የመዘናጋት ሁኔታ ጨርሶ መኖር የለበትም የምንለው። በበኩላችን በመጭው ጊዜ የሚልዮኖችን ኑሮ የሚያመሰቃቅሉና የሃገር ህልውናን ሳይቀር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ከባድ ከባድ የሆኑ ቀውሶች ይከሰታሉ የሚል ትልቅ ስጋት አለን። ከዚህ ተነስተን ወርቅማ ጊዜ ሳይባክን መልሶ ሚልዮኖችን የሚያንቀሳቅስ የጋራ ትግል ጎዳና ለመያዝ ካልሰራን ከታሪክም ዛሬ ካለንበት የውስጥም ሆነ የአለም አቀፍ ሁኔታ ምንም የቀሰምነው ትምህርት የለም ማለት ነው። ቅልበሳው ከቀጠለ ሃገራችንንና ህዝባችንን የሚጠብቃትን ፈተናና "ተያይዘው አንዱ እዛው በዛው ለሌላኛው መነሾም የሌላኛው መዘዝም እየሆኑ" የሚከሰቱትን የተቆላለፉ ቀውሶች ከየካቲት ቅልበሳ ማግስት ክስተቶች ጋር እያነፃፀርን ለውይይታችን ጥራት ሲባል ብቻ ከሶስት ከፍለን ለማየት እንሞክር።

## 1. የቅልበሳው መደርጀትና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዙሪያ ገጠም ቀውሶች አደጋ

የየካቲትን ቅልበሳ መዘዞች ዘወር ብለን ስንቃኝ ግንባር ቀደሙ ሃይል በሽብር ከተመታ በኋላ የታሰረው ታስሮ፣ የተረሸነው ተረሽኖ፣ ደብዛው የጠፋው ደብዛው ጠፍቶ፣ የተሰደደው ተሰዶ ቅልበሳው እየተደራጀና እየደረጀ ሲሄድ ህብረት እርሻ፣ መንደር ምስረታ፣ ሰፈራ..... እየተባሉ በተነደፉ የጥፋት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ሳቢያ ሃገራችን እንደ ቀይ ሽብሩ ዘመን በደርዘን ሽህ ሳይሆን ዘጠኝ መቶ ሽህ ድሃ ገበሬ ለፈጀው ለስመ ጥፉው "የክፍለ ዘመኑ ርሃብ"፣ ሁለት ሚልዮን ህዝብ ለስደት ለዳረገ አፈናና ትርምስ፣ ሌሎች ሚልዮኖችን ለእርዛት፣ ለሞትና ይህ ነው ለማይባል የኑሮ መመሰቃቀል ለተጋለጡበት የመከራ ምእራፍ ተዳርጋለች። ዛሬም ቢሆን ሌላ ነገር ሊኖር አይችልም።

ኢዴሃህ ምርጫ ዘመቻ ሲገባ ይፋ ባደረገው አማራጭ ሰነድ በሰፊው ከዘረዘራቸው ቀውሶች መሃከል ከእለት እለት እየሰፋና እየከፋ የሚሄደው መናጢ ድህነት፤ በከተማም በገጠርም እንዲሁ እየናረ የመጣው የጅምላ ስራ አጥነት፤ የጎዳና ተዳዳሪ ወጣቶችና ህፃናት ጉዳይ፣ 'ትውልድ ገዳዩ' የትምህርት ፖሊሲ፣ ሳይንስ ሊረሳቸው የቃጣቸውን የብሉይ ዘመን በሽታዎችን ጉዳይ ሳንፈታ የክፍለ ዘመኑ መቅሰፍት የሆነው ኤችአይቪ ኤይድስ ስለሚያደርሰው ጥፋት፤ የአካባቢ ውድመት ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። ቅንጅትም ቢሆን በነዚህ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ያለውን ህዝባዊ አማራጮች አቅርቦ ታግሏል።

እንደ የካቲቱ ማግስት ዛሬም የአለንበት የወከባ ሁኔታ ህብረተባችንንም እኛንም ወደ ተከላካይነት አውርዶን ፋታ ስለነሳን ምንም እንኳን እነዚህ ቀውሶች ዛሬም ከእኛው ጋር ቢሆኑና ከቅልበሳው ጋር እየተባባሱ ቢሄዱም እምብዛም የሚያነሳቸው የለም። በሽብርተኛና ማንኛዋንም የህዝብ ጥያቄ በአመፅ መደምሰስ ካለበት ተቃውሞ መለየት በማይችል አገዛዝ ስር እስከ ወደቅን ድረስ ከነዚህ ቀውሶች አንዱን ወይም ሌላውን መዘን እያወጣን ዛሬ "የእለት ጉርስ አጣን!" ነገ "ስራ ለስራ አጡ!" ከነገ ወዲያ ደግሞ "መናጢ ድህነት በቃን!" እየተባለ ብሶት ያለው ሁሉ በየበኩሉና በየተራው ብሶቱን እያነገበ መነሳት፣ መቃወም፣ ሰልፍ መውጣት የሚችልበትና በተናጠል ብሶት ወይም አጀንዳ ተናጠል ትግል የምናካሂድበት ሁኔታ ውስጥ አይደለንም። ኢዴሃህ ለግንቦት ምርጫ ባቀረበው አማራጭ ሰነዱ በዚህ ጉዳይ ያለውን እይታ ሲጠቁም፣

"ሃገራችን ባለችበት ዙሪያ ገጠም የቀውስ ጥምጥም ውስጥ እስካለን ድረስ ዛሬ ለአንዱ ችግር መፍትሄ አቅርበን፣ ነገ ሌላውን እንደ አመጣጡ ተጋፍጠን፣ ከነገ ወዲያ ደግሞ በተራው ያኛውን ችግር እንፈታለን ማለት ከአንድ ገደል ጫፍ ወደ ሌላ ገደል ጫፍ እያረፉ ለመዝለል እንደ መሞከር ያህል አደገኛ ህልም ነው። ጥረታችን ይህንን የጥፋት አዙሪት ለመስበርና ለአንዱ ቀውስ የሚቀርበው መፍትሄ ሌላውንም ችግር ለመፍታት ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት

የበጎ አዙሪት እምርታ ለመቀስቀስ መሆን ይኖርበታል። በአጭሩ ኢትዮጵያችን ከአለችበት ከባድ ቀውስ የምትወጣው ብሄራዊ ራእይ ባነገበ አጠቃላይና ሁለ-ገብ ስትራቴጂና እነዚህን የተቆላለፉ ቀውሶች በሙሉ በአንድ ሂደት ግንባር ለግን ባር ለመግጠም የሚያስችለን እንደ ችግራችን እሱም ሁለ-ገብና የተቀነባበረ እቅድ ስናቀርብና እኛም ህዝባችንም ለዚህ እውንነት ስንታገል ብቻ ነው።" በማለት ያለውን ሰፊና አገራዊ ራእይ በግልፅ አስቀምጧል።

"በተናጠል አጀንዳ ተናጠል ትግል" አይሆንም ማለታችን እነዚህን ከእለት እለት እየከፉና የህዝባችንን ጉረሮ አንቀው እየያዙ በሚሄድ ላይ ያሉ የቅልበሳው የኢኮኖሚና ማህበራዊ መዘዞች "ለጊዜው" ችላ እንበላቸው ማለታችን አ ይደለም። እንዲያውም ለማለት የምንፈልገው የዚህ ተቃራኒ ነው። የኢህአዴግ መሪዎች ህልም ሲሆን የግንቦት ድሎች ጉዳይ ጨርሶ ከኛም ከህዝባችንም አጀንዳ እንዲወጣ፤ ይህ ካልተሳካ ደግሞ የግንቦትን ቅልበሳ ግንቦት ሰባት በተደረገ ው የህዝብ ድምፅ ዝርፊያና በተከተለው የህዝብ ወገኖች አፈና ወስነንና ሚልዮኖችን እየቀጡ ያሉትን የኢኮኖሚና ማ ህበራዊ ፖሊሲዎች የመቃወሙን ነገር "ለጊዜው በይደር አስቀምጠን" ለፖለቲካና የመብቶች መከበርና ለዴሞክራሲያ ዊ ተቋማት መገንባት በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ ብቻ ትግል እናካሂዳለን እያልን እንድንኳትንላቸው ነው።

በተቃዋሚው ጎራ አንዳንድ ወገኖች የግንቦት ወንጀል የአማራጭ ዝርፊያም ገፅታ እንዳለው ጨርሶ በመሳት እ ዚህ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብለው የገቡ ይመስላል። ዝቅ ብለን በሰፊው እንደምንመለስበት ዛሬ ለሃገራችንና ለህዝባችን ያለው አንድ ከቀውስ የመውጫ ስትራቴጂ አዲስ ህዝባዊ ማእበል መቀስቀስና የኢህአዴግ መሪዎች ከያዙት የጥፋት ጉዞ እንዲገቱ ማስገደድ ብቻ ነው። ይህንን ካልን ደግሞ ህዝባዊ ማእበል ለመቀስቀስ ፊታችን የተደቀነው ትግል በፖለ ቲካውና በመብት ጥያቄዎች የሚያተኩር ግንጥል ትግል ከመሆን አልፎ ለምንና እንዴት በተዘረፋትም የኢኮኖሚና ማህ በራዊ አማራጮችና ከዚህም ጋር ተያይዘው በሚባባሱት የህዝባችን የህልውና ችግሮች ዙሪያ መደረግ እንዳለበት ለማብ ራራት እንሞክራለን። ከዚያ በፊት ግን ሃገራችን ላለችበት ሁኔታ የሚመጥን የጋራ ስትራቴጂ ስንነድፍ መጭው ትግል ከአሁኑ በባሰ የአቀበት ጉዞ እንዳይሆን በየካቲት አፍጠው አግጠው የተከሰቱና ዛሬም ብቅ ማለት የጀመሩ ሁለት ሌላ የ ቅልበሳ ማግስት መዘዞችን ስሌታችን ውስጥ አስገብተን እነሱንም ለመከላከል መታገል አስፈላጊ ስለሆነ በዚሁ በመዘዞ ች ጉዳይ እንቀጥል። ይህ ወደ ሁለተኛው የቅልበሳ መዘዝ ያመጣናል።

## 2. የግንቦት "መንፈስ" የመከሰምና የጨለምተኝነት አደጋ

አብዮትም ሆነ ማንኛውም ህዝባዊ እንቅስቃሴ እያየለ ሲሄድ የሚመዘገቡት ድሎች በተጨባጭ የኢኮኖ ሚ፣ ማህበራዊና የፖለቲካ ግኝቶች ብቻ የሚለኩ ድሎች አይደሉም። እነዚህን "ተጨባጭ" ድሎች እየቀደሙ፣ እ ያጀቡና እየተከተሉ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም እዚያው በዚያው ለነዚህ ድሎች እንደ-ቅድመ ሁኔታም እንደ ውጤት ሆነው የሚነግሱ ሌሎች "የማይጨበጡና የማይዳሰሱ" እሴቶች እንዳሉ የካቲትም ሆነ ግንቦት በግልፅ ያሳዩት ሃቅ ነው ። ትላንት "የየካቲት መንፈስ" ያልነው ዛሬ የቅንጅት መሪዎች "የቅንጅት መንፈስ" ሲሉ እኛ ደግሞ ከዚህ እጅግ አስ ፍተን "የግንቦት መንፈስ" ብለን የምንጠራው ይህ የህዝባዊ ትግል "የማይዳሰስ" ግኝት ምንድን ነው? በየካቲትም ሆነ በግንቦት አፍላ ወቅት ተከስቶ የነበረው ሚልዮኖች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለአንድ አላማ በአንድ አቅጣጫ የሚገፉበት፤ ትግግዝ፤ ከጀብደኝነት የሚዋሰን ጀግንነት፤ ከፀሃይ በታች የማይቻል ነገር የለም "ምን ጊዜም ወደፊት' እያለ ከድል ድል የሚያሸጋግር የማጥቃት ወኔ፤ ግለሰቡ እጣ ፈንታውን ከሚልዮኖች እጣ ፈንታ የሚያቆራኝበት፤ ከሁሉም በላይ ደ ግሞ የብሩህ ተስፋ ስሜት የሚገንኑበትና እነዚህ ሁሉ እርስ በእርስ እየተጋገዙ ያንን በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ህብረተሰብ ከዳር እስከ ዳር የሚያጥለቀልቁበት የበጎ አዙሪት "መንፈስ" ነው።

የዚያኑ ያህል ደግሞ ቅልበሳ የህዝብ ትግል ያስገኛቸውን ተጨባጭ ድሎች መልሶ በመንጠቅ አይወሰን ም። ቅልበሳ በማይታይና በማይዳስ ገፅታው በሚልዮኖች መንፈስ ትግግዝና ወንድማማችነት ከስመው "ከራስ በላይ ን ፋስ" የሚባልበት፣ ለሃገር ለወገን ለመሰዋት የሚገፋፋው የጋራ እጣ ፈንታ ጉዳይ "ለማን ብየ? ለምን ብየ?" በሚለው ራስ ተኮር ስሌት የሚተካበት፣ የአጥቂነት መንፈስ ቀርቶ ጥቃትን በወኑ የመከላከል ፍላጎት፣ አቅምና ቅስም እንኳን

ደብዛቸው የሚጠፋበት፣ ጀግንነት ከሞኝነት የሚቆጠርበት፣ የብሩህ ተስፋ ህልም ወድሞ በህብረተሰቡ ድቅድቅ ያለ ጨለምተኝነት የሚሰፍንበት የጥፋት አዙሪት ሂደት ነው።

በየካቲት በተጨባጭ በነበረው ሁኔታ ችግሩ ቀውሱ፣ መከራው እየከፋና እየተጠናከረ ሲሄድ የተነጠቁትን የህ ዝባችንን ድሎች መልሶ አስከብሮ በነሱ ላይ ለመገንባት ከፍተኛ ሚና ይጠበቅበት የነበረው የወጣቱ፣ የምሁሩ፣ የገበሬ ው፣ የሰራተኛውና በአጠቃላይ የካቲት አፍላ ላይ በአስደናቂ ጀግንነት ለአብዮቱ አላማዎች ሲዋደቅ የነበረው ግንባር ቀ ደም ሃይል "ፖለቲካና ኮረንቲ" በሚል የተሸናፊነት አባዜ ትጥቁን እየፈታ የመጣበት ሁኔታ ተከስቷል። በሰፈነው ጨለ ምተኝነት "ከደርግ የባሰ ምንም ሊመጣ አይችልም" በሚል ስሌት "እቃወማለሁ" የሚልን ሃይል ሁሉ የመናፈቅና ዞሮ ዞሮ ለወያኔ/ኢህአዴግ በር የከፈተ ስነልቡናዊ ሁኔታ ህብረተሰባችንን ተጠናውቶት እንደነበረ አይተናል። በአብዮቱ አፍ ላ ወቅት የነበረው የህዝቦች ወንድማማችነት ስሜት ላሽቆ በሃገር የመጣውን መአት በአንድነት ከመቋቋም ይልቅ ሁሉ ም ተስፋ ቆርጦ በየብሃሩ የሚከትበት አንጉል አቅጣጫም ሲያዝ ታዝበናል። የሰላም ትግል ራሱን የቻለ የጀግንነት ትግ ል መሆኑ ተረስቶ "ያለ ትጥቅ ትግል ስርየት የለም" ወደሚለው "ብቸኛ" የተባለ አማራጭ ተነጉዶ አገራችን የየካቲትን ድሎች በሚፃረሩና አንዳንዴም ደርግን ትተው እርስ በእርስ በሚፋለሙ ወደ ደርዘን በሚጠጉ የትጥቅ ትግሎች ስትጥ ለቀለቅና ስትደማ አይተናል።

ዛሬም ይህ የጨለምተኝነት አባዜ አይን ላለው ሁሉ የሚታይ ነው። ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ በአንዳንድ ወገኖቻ ችን በህዝባዊ ትግሎች የአፍላና የአጥቂነት ዘመን የተንፀባረቁትን በጎ ግኝቶች እንደ "ዘላለማዊ" አድርጎ የመቁጠር ች ግር እንዳለ የዚያኑ ያህል ግልፅ ነው። እንደዚህ አይነቱ የህብረተሰቡን የትግል ቅስም መሰበርና የትጥቅ መፍታት ሂደት እውነታ መካድና ይህንን ክስተት ስሌት ውስጥ ሳያስገቡ የትግል ስትራቴጂ ለመንደፍ መነሳት ለቀጣዩ ትግል ቢያንስ ሶ ስት ችግሮች አሉት።

የትግል አፍላ ዘመንን ወኔ ዘልአለማዊ አድርጎ መውሰድ የሚያመጣው የመጀመሪያው ችግር የህብረተሰቡ ን ለገጠሙት ቀውሶች አፀፋ የመስጠት ያለውን አጋንኖ የማየትና የትግል ስትራቴጂንም በዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ ተመር ኩዞ የመንደፍ ችግር ነው። በየካቲት ማግስትም ሆነ አሁን በግልፅ እንደምናየው ብዙ ወገኖቻችን በአንድ በኩል በቀው ሶች እየከፋና እየተበራከቱ መሄድና በሌላ በኩል ደግሞ ህብረተሰቡ ለነዚህ ቀውሶች "ጤናማ" የሆነ አፀፋ ለመስጠት በሚያሳየው ፍላጎትና አቅም መሃከል ያለውን ዝምድና በትክክል ያለማጤን ችግር ያለባቸው ይመስለናል። ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት በወረደ ህብረተሰብ ውስጥ የችግርና ግፍ መበራከት ብቻውን እያየለ የሚሄድ ህዝባዊ ተቃውሞ አይስ ነሳም። በእንዲህ አይነቱ ህብረተሰብ በቀውስና በህዝባዊ አፀፋ መሃከል ያለው ዝምድና እንዲያውም የዚህ ተቃራኒ ነው ። በተለይ ለሁኔታው የሚመጥን አመራር በሌለበት ሁኔታ ከቀውሶች መበራከት ጋር ህብረተሰቡ ጤናማ አፀፋ ለመስጠ ት ያለው አቅም እየሟሸሸ እንደሚሄድ በየካቲት ማግስት በግልፅ አይተነዋል።

ከየካቲት ቅልበሳ እስከ ውድቀቱ ባለው ወቅት ደርግ ባፈራረሳቸው ህዝባዊ ተቋማት መቃብር ላይ ኢሰፓ ፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሰራተኞች እያለ የራሱን መዋቅሮች ሲተክል ሃገራችንና ህብረተሰባችን "የተደራጁ" ይመስሉ ነበር። በየጊዜው "ለአብዮትና ለእናት አገር" እየተባለ ከአዲስ አበባ እስከ ዳር ድንበር መንደር ሰልፎች ስለተወጣ ህብ ረተሰባችን ሃገሩን፣ ኑሮውን በተመለከተ የትግል ወኔው ያልተነካ ይመስለን ነበር። ነገር ግን ሂደቱ ሃገርንና ህብረተሰብን የማፈራረስ፣ የህዝብን ቅስም በሽብር የመሰባበር ሂደት ስለነበረ ወያኔ/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በአሸዋ ላይ የተገነቡት ተቋማት እንደ እንቧይ ካብ ፈራረሱ። የአስራ አራት አመቱ የቅልበሳ ሂደት የህብረተሰባችን የአፀፋ መስጠት ፍላጎቱና አቅሙ እየሟሸሸ የሄደበት ስለነበረ ሌላው ቀርቶ አዲስ አበባ ተቀምጦ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ነኝ የሚል ሃ ይል ኤርትራን አስገንጥሉልኝ ብሎ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማመልከቻ የማስገባትን ያህል ወንጀል ሲፈፅም ህ ዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ "ሆ" ብሎ ለተቃውሞ የሚነሳበት ሁኔታ ውስጥ አልነበረም።

ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ ዛሬ በርካታ ወገኖቻችን የትግል ስትራቴጂያቸውን ሲነድፉ የቀውሶች መከፋት " አይቀሬ" የሆነ ህዝባዊ ትግል ይጋብዛል ከሚል ህልም የሚነሱ ይመስላል። ይህም በመሆኑ ላለው ቀውስ ለታጋዩ ህዝብ ግልፅና ቀላል አማራጭ አመልክቶ፤ ለዚህ ትግል አስፈላጊ የሆነውን የጋራ አቅጣጫ ይዞና የጋራ መድረክ ፈጥሮ ታግሎ የማታገሉ ጉዳይ ወደ ጎን ይተዋል። ከዚህ ይልቅ የተቃውሞው "ተጋድሎ" አልፋም ኦሜጋም የፀረ ህዝቦቹን የማያባራ

ግፍ ''አጉልቶ በማሳየት'' ለቀባሪ ለማርዳት በሚግደረደሩና ''አትርሱን'' በሚል መልክ ተቃውሞን ''ለማስመዝገብ'' በ ሚበተኑ፣ ህዝባችንን ነጋ ጠባ ተነስ ታገል እያሉ በሚወተውቱ መግለጫዎችና 'ሰበር ዜናዎች' የሚወሰንበት አደጋ ይከሰ ታል። ይህ አይነቱ አካሄድ ለቀልባሾቹ ፋታ ከመስጠት ሌላ የሚፈይደው ምንም ቁም ነገር የለውም።

ሁለተኛ ይህንን የህዝባዊ ትግል ወቅት ''መንፈስ'' ዘልአለማዊ አድርጎ መቁጠር ይህ ግኝት ጨርሶ እንዳይወድ ም እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ካለመገንዘብ የሚመጣ ችግር ነው። ይህ ደግሞ ዛሬ ኢህአዴግ በአመፅ ሊደመስሰው የተነሳውንና ከጦር የሚፈራውን የህዝብ የትግል ወኔ እየተፈታተኑ የመክሰሙን ሂደት የሚያግዝ አዝማሚያ ሊያስይዝ እንደሚችል በግልፅ እያየን ነው።

በአንድ በኩል ከአንገት በላይ በሚመስል መልክ ህዝባችንን ''እንደ አንድ ሰው ሆነህ ተነስ'' እያልን በሌላ በኩ ል ደግሞ ከህዝባችን ችግር አንፃር ''እዚህ ግቡ'' በማይባሉና ዞሮ ዞሮ ደግሞ ''ተነስ ታገል'' ለሚባለው ህዝብ በማይጨ በጡ ልዩነቶች የመከፋፈል አባዜ አለ። ከእንዲህ አይነቱ እጅ እጅ እስኪለን ድረስ በተደጋጋሚ ካየነው የግንባር ቀደም (ወይም ግንባር ቀደም ነን ባይ) ሃይሎች መከፋፈልና መቦጫጨቅ በስተ ጀርባ ያለውንም ''ሎጂክ'' ሆነ ከሱ የሚከተለ ውን ሂደት ጠንቅቀን እናውቀዋለን። ''ሎጂኩ'' ህዝብ አክ እንትፍ ብሎ የተፋውን ሃይል የእኔ ድርጅት በወጉ እንዳይፋ ለመው ታጋይ መስሎ ከጎኔ የቆመው ድርጅት ወይም አንጃ ''እጅ እግሬን አስሮ ይዞኛል'' በሚል ሰበብ ዋናውን ጠላት '' በወጉ ለመፋለም'' በቅድሚያ ይህንን ዳንቀራ ማስወገድ ያስፈልጋል በሚል በቀጥታ ''ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው/አ ስቀድሞ መምታት አሾክሿኪውን ነው!'' ከሚለው ከቀድሞ ፊውዳል ስርአት የተወረሰ ''የትግል ሎጂክ'' ነው። ውጤቱ ስ? እንዲህ አይነቱ ስሌት በአንድ በኩል ከዋናው ባላንጋራ ጋር የተያዘውን ትግል ''በይደር'' የማስቀመጥና ለጊዜው ት ግሉ ''በአሾክሿኪውና በከሃዲው'' ላይ የማተኮር አቅጣጫ ተይዞ ሁሉም ''እየተጋገዘ'' የድክመት አዙሪት የሚገባበት ሁ ኔታ ይፈጠራል። በሌላ በኩል ደግሞ በቋፍ ባለው ህብረተሰብ ውስጥ ''ሁሉም ያው ናቸው'' ከሚል የሚመነጨውን የ ጨለምተኝነትና የትጥቅ መፍታት ሂደት እያገዙ በቀጥታ የገዥዎችን የህዝብ ቅስም መስበር ስትራቴጂ ማገዝ ይሆናል ።

ሶስተኛው ችግር ከዚሁ ከግንባር ቀደም ሃይሎች መቦጫጨቅ ጋር ተያይዞ ብቸኛና ከሁሉ ይበልጥ ቁርጠኛ ታ ጋይ መስሎ ለመታየት ሲባል ብቻ የሚወረወሩ በተጨባጩ የህብረተሰቡ ሁኔታ ለጊዜው ''ከአቅም በላይ'' የሆኑ የትግል ጥሪዎችን የማስተላለፍ ችግር ነው። እንደዚህ አይነቶቹ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በአጉል ግንባር ቀደሞች የሚስተጋቡት የትግል ጥሪዎች ይህንን የትጥቅ መፍታትና የጨለምተኝነት ሂደት የሚያግዙበት ሁኔታ እንዳለ መረዳት ያስፈልጋል። ይህ አባባላችን ግልፅ እንዲሆን መስከረም 1998 እ.ም. በሃገራችን ተጠርቶ የነበረውን የሶስት ቀና ት የቤት መዋል አድማና ከአመት ተኩል በፊት በአለም አቀፍ የቅንጅት አመራር ለተማሪዎችና በአጠቃላይ ለኢትዮጵ ያ ህዝብ የተደረገውን የትምህርት ማቆምና የቤት መዋል አድማ ጥሪ ማነፃፀር ይበጃል።

የመስከረም 98ቱ ጥሪ በግንቦቱ እምርታ እየታገዘ ገና በአጥቂነት ደረጃ ለነበረ ህብረተሰብ ተፋፍሞ ይካሄድ የነ በረ እንቅስቃሴውን ይበልጥ አፋፍሞ እንዲቀጥል የተደረገ ትክክለኛና ወቅታዊ የትግል ጥሪ ነበር። እነ አቶ መለስ፤ አን ዳንድ የህብረቱና የቅንጅት መሪዎች እንዲሁም ዲፕሎማቶች በድርድር በሰላምና መረጋጋት ስም ተመሳጥረው ባያከሽ ፉት ኖሮ ሚልዮኖች እንደ አንድ ሰው ሆነው የደገፉትና ሙሉ በሙሉ የሚሳተፉበት አድማ ነበር። ይህ ጥሪ የህዝብ ት ግል መፋፋም በሚያስደነግጣቸው ሃይሎች ትብብር መሰረዙና ህዝቡ ያምናቸው በነበሩ መሪዎቹ የነብር ጭራ እንዲይ ዝ ከተደረገ በኋላ መልሶ እንዲለቅ በመደረጉ ለቀጣዩ ትግል መፍዘዝና ዛሬ ላለንበት አስከፊ ሁኔታ ወሳኝ የሆነ አሉታዊ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ማንም የሚክደው አይደለም።

ውጭ ባሉት የቅንጅት መሪዎች የተደረገው ጥሪ ''በምኒልክ ዘመን የደነቆረ......'' እንዲሉ በቀደሙት ወራት እ የሰፈነ የመጣውን ''የግንቦት መንፈስ'' የመፍረክረክ ሂደት ጨርሶ ሳያገናዝብ፤ ምንም አይነት ምክክርም ሆነ ዝግጅት ሳ ይደረግበት ሰኞ ለሚጀመር አድማ አርብ ቀን ''በአወጣ ያውጣው'' ተብሎ የተወረወረ አጉል ግንባር ቀደምትነትን የሚያ ንፀባርቅ አደገኛ ጥሪ ነበር። አሉታዊ ውጤቱ ጥሪው ከተደረገለት ከህዝባችን በኩል የአወንታዊ ምላሽ የጅማሮ ጅማሮ

እንኳን ባለማግኘቱ ብቻ የሚወሰን አልነበረም። እንዲህ አይነቱ ሃላፊነት የጎደለው "የትግል ጥሪ" አይቀሬው መክሸፍ ሲከሰት በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ተስፋ መቁረጥ እያገዘ በቀጥታ ለወያኔ/ኢህአዴግ የሚሰራ ስትራቴጂ ነበር። የሆነውም ይኸው ነው።

ይህ ማለት ግን ከእንግዲህ ነገሩ ሁሉ አልቆለታል በሚል እኛም በጨለምተኝነት ተውጠን ትጥቃችንን እንፍታ ለህዝባችን የትግል ጥሪ አናስተላልፍ ማለት አይደለም። የሃገራችን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎች ሁሉ መክረውና ዘክረው ለአለው ሁኔታ የሚመጥን "ጤናማ" የሆነና ህብረተሰቡ ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ዝቅ ብለን በምንጠቁመው ተአማኒነት በገነባ አመራር በሚኒደፍ የጋራ ስትራቴጂ ታግለው ለማታገል ይንቀሳቀሱ ማለት ብቻ ነው። ደጋግመን ስለ "ጤናማ አፀፋ" ያወሳነው ትላንት ከየካቲት ውድቀት ከቀሰምነው መራራ ትምህርት ተነስተን ነው። የየካቲት ሃይሎች ሃገራችን ከነበረችበት የቀውስ አዙሪት ዴሞክራሲን፣ ብልፅግናን፣ አንድነትን፣ የብሄሮች እኩልነትንና ወንድማማችነትን፤ ፍትህንና ብሄራዊ ነፃነትን በአጭሩ የአብዮቱን እሴቶች መልሶ ለማንገስ ለቅልበሳው የሚመጥን አፀፋ መስጠት አለመቻላቸው የትግሉን መክሰም አላመለከተም። ዛሬም ቢሆን በግንቦት ማግስት ይህንን ታሪካዊና ህዝባዊ ድል መልሶ ህዝባችን እጅ ለማስገባት በሚለው መንፈስ የሚካሄደው ተጋድሎ በዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ብቃት ማነስ ቢዝረከረክ ትግሉ ይቆማል ማለት አይደለም። ይህ ደግሞ "የአጉራል አፀፋ አደጋ" ወደምንለው የቅልበሳው ሶስተኛ መዘዝ ያመጣናል።

## 3. የአጉራል አፀፋና የትርምስ አደጋ

የአብዮትም ሆነ የሌላ የህዝብ እንቅስቃሴ ያስገኛቸው ድሎች በቀልባሾችና በፀረ ህዝቦች ሲነጠቁ ህብረተሰቡን ወደ እነዚህ ድሎች የመሩት ግንባር ቀደም ሃይሎች ቅልበሳውን ለመመከት የሚያስችል ብቃት ካላሳዩ ትግሉ ከነዚህ ድሎች ጋር ምንም ግንኙነት በሌላቸውና እንዲያውም ህብረተሰቡ ድሌ የሚላቸውን እሴቶችና ግኝቶች አጣጥለውና ተፃረው በሚነሱ የውስጥ ሃይሎችና ባእዳን እንደሚጠለፍ የካቲት በግልፅ አሳይቶናል። እንዲህ አይነቱ የአጉራል አፀፋ አካሄድ ሁለት የተያያዙ ገፅታዎች አሉት። በሃገር ደረጃ ድሮውንም ቢሆን ድሎቹን ባስገኘው ህዝባዊ እንቅስቃሴ የሚረባ ተሳትፎ ያላደረጉና አልፎ ተርፎም በዚህ ትግል ጠርዝ ላይ (ማርጅናል) የነበሩ ሃይሎች ከቅልበሳው ጋር በመድረኩ ላይ ዋና ተዋንያን ሆነው ብቅ የሚሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። በአካባቢና በአለም አቀፍ ደረጃም በህዝባዊው ትግልና በድሉ ወቅት "የት ነበሩ?" የሚባሉ የውጭ ሃይሎች በመድረኩ ላይ መአከላዊ ቦታ የሚይዙበትና ከእነዚህ ባእዳን አንዱ ከመንግስት ሌላው ከተቃዋሚ ጋር ወግነው በሃገራችን የውስጥ ጉዳይ ገብተው የሚፈተፍቱበትና ህብረተሰቡን የሚያተራምሱበት ሁኔታ ይፈጠራል።

የካቲትን በተመለከተ የውስጥ አጉራል አፀፋ ለምንለው ሂደት እንደ ዋና ምሳሌ ሊወሰድ የሚችለው በህዝባዊው ትግልና ድል ወቅት ምንም አወንታዊ ሚና ያልነበረው ህወሃት በይፋ ሲያንፀባርቅ የነበረው አቋም ነው። መጀመሪያ በደምና በመስዋእትነት የተገኙትን ህዝባዊ ድሎች እንዳልነበሩ አድርጎ የማጣጣልና የመካድ አባዜ አለ። ታላቁ የየካቲት የመሬት አዋጅ ምን ነበር? በህወሀት መሪዎች አባባል ይህ የሃገራችን ድሃ ገበሬዎች አይከፍሉ መስዋእትነት እየከፈሉ እውን ያደረጉት ስር ነቀል ፀረ ፊውዳል አዋጅ "ንኡስ ከበርቴ መኮንኖች" የህዝቡን ጥያቄ "ለማድበስበስ" የሰነዘሩት "ጥገናዊ" እርምጃ ነበር!!

"በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ በየአካባቢው ከርረው የታዩት ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ህዝቡ በግብታዊነት ተነሳስቶ የሃይለስላሴን ፊውዶ ቡርዥዋ መንግስት አንኮታኩቶ ለመጣል አብቅቶታል። ይሁን እንጂ ከፍተኛውን የንኡስ ከበርቴ መደብ የሚወክለው የወታደራዊ መኮንኖች ቡድን አብዮቱን በማኮላሸት ስልጣን ላይ ሊወጣ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ይህ ቡድን ራሱን ወደ ተሟላ ከበርቴነት ለማሳደግ ተቀናቃኞቹ የነበሩትን የቀድሞ ገዥ መደቦች ለማዳከም የህዝቡም አብዮታዊ ትግልና ግፊት ደጋፊ መስሎ በመቅረብ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ሲል የተወሰኑ ጥገናዊ ለውጦችን ለማድረግ ተገደደ። በተለይ በዚያን ጊዜ እጅግ አንገብጋቢ የነበረውን የመሬት ጥያቄ ለማድበስበስ ያቀረበው የመሬት

አዋጅ በአብዮቱ ሰፈር ውስጥ ትልቅ ውዥንብር ያስከተለ አዋጅ ስለነበረ በምሳሌነት መጠቀስ ያለበት ነው።"_( የትግል ጥሪ ቅፅ 1 ቁ. 2 መጋቢት 1977 እ.ም. )

አንጉል አፀፋ የምንለው ክስተት የህዝቦችንን የመሰዋእትነት ፍሬ እንደዚህ በማጣጣል አይወሰንም። ከዚህ ተያይዞ የአብዮቱ ትግልና ድል የሚገባውን ሁለተኛ ደረጃ አስይዞት የነበረውን የብሄር ጥያቄ የሃገሪቱ ህዝቦች "ዋና" የትግል አጀንዳ ሆኖ ለማቅረብ ይሞከራል። አይን በሚያወጣ መልክ የየካቲትን ድሎች "ጥገና ለውጥ" ብሎ የሚያጣጥለው የወያኔ "ኮሙኒስት ሃይል" አሁንም አይን በሚያወጣ ሸፍጥ በየካቲት አፍላ ጊዜ ግንባር ቀደሙ ሃይል የዚህ ወይም የዚያ ብሄር ሳይል በኢህአፓም በመኢሶንም በሌሎች ህብረ ብሄር ድርጅቶች ስር እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድነት እንዳልታዋደቀ፣ አብዮቱን የሚቃወሙ ሃይሎችም በበኩላቸው ብሄርና ጎጥ በሚል ዘይቤ ሳይከፋፈሉ በአንድነት ተቃቅፈው ይህንን ሂደት ለመቀልበስ በጋራ እንዳልታገሉ ሁሉ ይህንን በጎ ክስተት እንዳልነበረ አድርጎ በሬ ወለደ ከሚተርክባቸው ሰነዶች አንዱን ብንጠቅስ፣

"የህወሃት ኮሙኒስት ሃይል ከመጀመሪያው ጀምሮ በኢትዮጵያ አብዛኛው ህዝቧን የሚመለከት እጅግ የከፋ ብሄራዊ ጭቆና የነበረና የአለ መሆኑን፣ የዚህ ብሄራዊ ጭቆና መንስኤ በፊውዳሊዝም፣ በኢምፔርያሊዝምና በቢሮክራሲ ካፒታሊዝም የሚካሄደው መደባዊ ጭቆናና ብዝበዛ መሆኑን፤ ከየካቲት 1966 እ.ም. በፊትም ፣ በየካቲትም ይሁን ከዚያ በኋላ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ተብቶ የሚታየው ቅራኔ የብሄር ቅራኔ መሆኑን፣ ስለሆነም የኢትዮጵያ ዋነኛ ቅራኔ የብሄር ቅራኔ መሆኑን ያምን ነበር። አሁንም ያምናል። ይህ አሁንም ያኔም ትክክለኛ አቋም ነው።" (የህወሃት ኮሙኒስት ሃይል የአስር አመት ጉዞ ግምገማ - በማሌሊት መስራች ጉባኤ የፀደቀ - ሃምሌ 1977 እ.ም.)

ይህ ለታሪክ የሚተው አንጉል አካሄድ አይደለም። በግንቦትም ማግስት በተለይ "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ" የተባለው ከአምስት አባላቱ አራቱ በግንቦቱ ትግልም ሆነ ድል ባልተሳተፉ ድርጅቶች ከተመሰረተ ወዲህ በግልፅ እየታየ በሜዳ ላይ ያለ አካሄድ ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ኢዴሃህ) በዩትሬክት በተመሰረተው በዚህ ድርጅት አባል ከመሆን የተቆጠበበት አንዱ ምክንያት ከዚህ ስብስብ መሰራቶች ጋር በግንቦት ድሎች ጉዳይ የተንፀባረቀው ልዩነት እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ስብስብ "የግንቦት ድሎችን የማስመለስ" ሃሳብ ቀርቶ የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦት 97 ተጎናፅፏል የምንላቸውን ድሎች እንኳን ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ስብስብ ነው። ትላንት ወያኔ የየካቲቱን ተጋድሎ "በጥገና ለውጥ" ግርግርነት እንዳሰናበተው ሁሉ የኦነግ ቃል አቀባይ አቶ ሌንጮ ባቲ "ማለዳ" በተባለ መፅሄት በግንቦቱ ምርጫ ጉዳይ የድርጅታቸውን አቋም ሲያስረዱ

" ከኦሮሞ አንፃር ስናየው የተደረገው ምርጫ የኦሮሞን ህዝብ ያላካተተ ምርጫ ነው። ..የኦሮሞ ህዝብ ነፃ ሆኖ የሚፈልገውን ፓርቲ የሚመርጥበት ሁኔታ አልነበረም።" ካሉ በኋላ እኛ ህዝባችን በምርጫው ዘመቻ ወቅት በሚልዮን እየተቆጠረ ተንቀሳቅሶ፣ በምርጫው ቀን በነቂስ ወጥቶ ድምፁን ከሰጠና ድል ከተጎናፀፈ በኋላ የኢህአዴግ መንግስት ይህንን ድሉን በአመፅ ከጁ ነጠቀው ብለን "ስለቅልበሳ" እያወራን እሳቸው ደግሞ " ነፃና የኦሮሞ ህዝብ ፓርቲዎች አገር ቤት ውስጥ በነፃ ተንቀሳቅሰው ያላቸውን ፕሮግራምና አላማ ለህዝቡ ገልፀው የሚቀርቡበት ሁኔታ አልነበረም።" ይሉናል። ("ማለዳ" ቅፅ 1 ቁጥር 5 ሃምሌ 1998 እ.ም.)

ይህ አንጉል አካሄድ በዚህ አይወሰንም። በግንቦት ንቅናቄ ሳቢያ ህዝቦች ለአስራ አራት አመታት የተጠመደላቸውን የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ አክሽፈው አማራው ለአማራ፣ ኦሮሞው ለኦሮሞ፣ ትግሬዩ ለትግራይ፣ ጉራጌው ለጉራጌ፣ ክርስቲያኑ ለክርስቲያኑ-፤ ሙስሊሙ ለሙስሊም ሳይሆን እንደ አንድ ሰው ለዴሞክራሲና ለአንድነት ድምፃቸውን እንዳልሰጡ ሁሉ ዛሬም የዚህ አጉል አካሄድ ጠበቆች እንደ ገና መልሰው የሚሰልቁት በየካቲት ታልፎ ሄዶ እንደነበረው በግንቦትም ታልፎ የሄደውን "የብሄር ጥያቄ ዋናነት" ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ከኦነግ አመራር እንዲያውም በትብብሩ ውስጥ የድርጅቱ ተወካይ ናቸው የሚባሉት ዶ/ር በያን ሁሴን በመስከረም ወር 1999 እ.ም. በሰጡትና በየድህረ ገፁ ወጥቶ ብዙ ባለጋገረ ቃለ ምልልስ ሊያስረዱን የሞከሩት ይህንን "እውነታ" ነበር። እኚህ ተወካይ ብሄርና ህብረ ብሄር የሚለው ክፍፍል የማያስኬድ እንደሆነና "እውነቱን ለመናገር ከተፈለገ" የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁሉም የብሄር ፖለቲካ እንደሆነ ተናግረው "መኢህድ የነበረው ድርጅት ስሙን 'መላ ኢትዮጵያ' ስላለ ብቻ የብሄር ፍላጎትን ማንፀባረቅ አቆመ ማለት እንዳይደለ እየተነተኑ ለማስረዳት ሞክረዋል።

በህዝባዊ አንቅስቃሴዎች ሽንፈት ማግስት እንዲህ አይነቱ ክስተት ብቻውን አይመጣም። የካቲት ያረጋገጠልን ም ሆነ ዛሬ በግንቦት ማግስት እያየን ያለነው ሌላ አደጋ ህዝቦች ድሎቻውን በአመፅ ሲቀሙ በአጠቃላይ የእጣ ፈንታቸ ው ጉዳይ ከእጃቸውና ከቁጥጥራቸው ውጭ እንደሚወጣና ከህልማቸውና ከጥቅማቸው ምንም ግንኙነት ለሌላቸው ድን በር ዘለል ትርምሶች እየተማገዱ የደምና የእንባ ግብር ለመክፈል የሚገደዱበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ነው።

በደርግ ዘመን በ1969 እና 1970 እ.ም. ስለተካሄደው "የሱማሌ ወረራ" ጉዳይ ሲነሳ ብዙ ወገኖች ይህ ጦርነት ከቅልበሳው ጋር ያለው ጥብቅ ግንኙነት አይታያቸውም። ለሶስት አመታት ያህል ከድል ወደ ድል እየተሸጋገረ ይጓዝ የነ በረው የየካቲት አብዮት የኢትዮጵያ ህዝብ የማንንም የውጭ ሃይል እገዛ ሳይጠይቅም ሳያገኝም በራሱ ትግልና መስዋእ ትነት ብቻ ያስመዘገበው አንጡራና አኩሪ ግኝቱ ነበር። ቀደም ሲል ይህንን አብዮታችንን "ማኦይስት" ብለው በመፈረ ጅ በጥርጣሬ አይን ሲያዩና አልፈው ተርፈው በህዝባችን ትግል ላይ ሲያሻጥሩ የነበሩት የሶቭየት ተስፋፊዎች በጥር 26 1969 እ.ም. የኮለኔል መንግስቱ መፈንቅለ መንግስት ማግስት 'አብዮቱን ለማገዝ' በሚል ሰበብ ከአብዮታዊ ሰደድ ወግን ው ቅልበሳውን ለማጠናከር ወደ ሃገራችን ገቡ። መኢሶን በመጋቢት ወር 1969 እ.ም. ከዛ ከታላቁ ምሁር ሃይሌ ፊዳ ብእ ር በወጣና ከሰደድ መሪዎች ጋር ብዙ ባወዛገበ 'የሰፊው ህዝብ ድምፅ' እትም ቁጥር 53 ደርግ እየተሰማራ ስላለበት ፖለ ቲካ አደገኛነት ሲያስጠነቅቅ፤

" የሶሻሊስት አገሮችና የሌሎችም የአለም ተራማጅ ሃይሎች ድጋፍ መገኘት ለኢትዮጵያ አብዮት በጣም አስ ፈላጊና ሲገኝም ደግሞ በጣም አስደሳች ነገር ነው። ይሁንናም በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ቢሆን፤ ምን ያህል ኢኮኖሚያ ዊ፤ ፖለቲካዊና የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ቢኖሩም፤ የፈለገውን ያህል አብዮታዊ በአድሃርያን ጥይት ቢወድቅም፤ ባጭሩ ማንኛውንም መስዋእትነት ቢጠይቅና ትግሉ የፈለገውን ጊዜ ቢፈጅም አብዮታውያን ከሁሉም በላይ መተማመን ያለባ ቸው በሃያ ስምንቱ ሚልዮን የኢትዮጵያ ህዝብና በኢትዮጵያ ምድር ሃብት ላይ ነው። ከዚህ አይነቱ እምነት መዛነፍ የ መጣ እለትና ተስፋችንን በውጭ ሃይሎች ላይ መጣል ያመጣን እለት የተኮላሸ አብዮትና 'በነፃነት ለዘልአለም ትኑር' የ ተባለችው አገራችን ተመልሳ ከባርነት ስር የምትወድቅበት ቀን እንዲመጣ ማገዛችን እንደሆነ መታወቅ አለበት።"

ይህ አዲስ ክስተት ጭንቀት የፈጠረው በኢትዮጵያ አብዮታውያንና አገር ወዳድ ሃይሎች ሰፈር ብቻ አልነበረ ም። በነበረው የቀዝቃዛው ጦርነት ሁኔታ (ኮንቴክስት) ለኛ የአብዮታችን መቀልበስና የብሄራዊ ነፃነታችን መደፈር አደ ገር ያዘለው ጣልቃ ገብነት ለምእራቡ አለም ደግሞ የሶቭየት ተስፋፊዎች በአፍሪካ ቀንድና ስትራቴጂክ በሆነው ቀይ ባ ህር አካባቢ የሚተከሉበት አደገኛ ሁኔታ ፈጠረ። በጥር ሃያ ስድስቱ መፈንቅለ መንግስት አማካኝነት ኮለኔል መንግስቱ ስልጣን ጠቅልለው ፊዴል ካስትሮ ድጋፋቸውን አዲስ አበባ መጥተው በሰጡ ማግስት በቀደሙት አመታት ለምእራቡ አለም "የሞት ሽረት" ጥያቄ ያልነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ እንቅስቃሴ ገፅታ ሙሉ በሙሉ ተቀየረ። በየካቲት ወር 1969 በአዲሱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ካርተር በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካይ ሆነው የተሾሙት አምባሳደር አንድሪ ው ያንግ ስራቸውን በኒው ዮርክ ሲጀምሩ ባደረጉት የመጀመሪያው ጋዜጣዊ ጉባኤ ስለተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ሲተቹ፤

" በአፍሪካ ቀንድ በመጠንሰስ ላይ ካለው ቀውስ ጋር ሲነፃፀር በደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል - ማለትም በአንጎላ፣ በሞዛምቢክ፣ በናሚብያና ዚምባብዌ - የሚካሄደው ሁሉ ለአለም ሰላም በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው።" በማለት ከእ ንግዲህ ሃገራችን የቀዝቃዛው ጦርነት "የተሟሟቀ ግጭት" የሚካሄድባት ምድር ልትሆን የምትችልበት አደጋ እንዳለ አስታወቁ።

የመኢሶንም የአሜሪካው አምባሳደርም ማስጠንቀቂያዎች ተሰንዝረው መንፈቅ ሳይሞላቸው እኛ እንደ ቀላል ነገ ር 'የዚያድ ባሬ ወረራ' የምንለው በተጨባጭ ግን በወቅቱ አንድ የምእራብ ጋዜጣኛ እንደታዘበው ከቅርብም ከሩቅም " ከአለም አገሮች ግማሾቹ ያህል ወገን ለይተው የሚፋለሙበት" የኦጋዴን ጦርነት ተጀመረ። የኢትዮጵያ ህዝብም በእን ቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንደሚባለው የአብዮቱን ፍሬ መነጠቁና ብሄራዊ ነፃነቱንና ክብሩን መቀማቱ ሳያንሰው በሃያላን መካከል የሚካሄደው ግጭት ውስጥ ገብቶ የሚዳክርበት አስከፊ የታሪክ ምእራፍ ተከፈተ።

ዛሬም በግንቦት ቅልበሳ ማግስት እየታዘብን ያለው ይኸው ነው። ትላንት "የአብዮታዊ ሰደድ" መሪዎች ምንም የማይመለከተን የቀዝቃዛው ጦርነት "አርበኞች" ሆነው በ"አሜሪካን ኢምፔርያሊዝም" ላይ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀ ፍ ኮሙኒስት እንቅስቃሴ ውስጥ እንኳን ወገን ለይተው ጣልቃ በመግባት "በቻይና ከላሾች" ላይ እንዘምታለን ብለው ሲ

ግደረደሩ ለነሱ እያፈርን ታዝበን ነበር። ዛሬም ቀልባሾቹ እነ አቶ መለስ ዜናዊ በፀረ ሽብሩ ''አጠቃላይ ጦርነት'' በወራ
ዳ ቅጥር አርበኝነት ተሰልፈው ሃገራችንን ለማሰላሰል እንኳን ለሚዘገንን አደጋ እያጋለጧት እናያለን። በህዝብ የተጠሉ
ና የተተፉት ቀልባሾች በውስጥ ያጡትን ድጋፍ ለባእዳን በማደር ለማካካስ ሲሞክሩ በነዚህ ባእዳን ''ጃስ'' ተብለው በ
ሱማሊያ በማካሄድ ላይ ያሉት ጣልቃ ገብነት ከነ መለስ ዜናዊና ከሱማሊያ የጦር አበጋዞች አልፎና ዘልቆ የሚሄድ ሰፊ
ገፅታና መዘዝ እንዳለው ለማንም ግልፅ ነው። ዛሬ እድሜ ለኢህአዴግ መሪዎች በአረብያ መቆሚያ መቀመጫ አጥተ
ው ለነበሩ ለእስልምና ሃይማኖት ቀዳማይ ተከታዮች ጠለላ ሰጥታና መከታ ሆና ከመከራ ያተረፈችና ነብዩ መሃመድ ''
ማንም የማይበደልባት የፃድቃን ምድር'' ብለው ያከበሯት ሃገራችን በጥቂት ቅጥረኞችና የታሪክ ድንኮች ሴራ እንደ ስ
መጥፉው ጓንታናሞ ቤይ ''የእስላም ሽብርተኞች'' እስር ቤትና የሰቆቃ ምድር ሆናለች። በቅርቡ አምኒስቲ ኢንተርናሽና
ል እንደ ዘገበው በሱማሊያ ምድር በዚች አገራችን ስም የሚንቀሳቀሱ ወታደሮች መስጊድ እየደፈሩ ምእመናንን የሚያ
ርዱበት አስከፊ ምእራፍ ደርሰናል። በዚህ ለዚች አገራችን ብሄራዊ ክብርም ሆነ ለደህንነቷ አደገኛ በሆነ ፀረ ህዝብ ሴ
ራ ምክንያት የእስልምና ሃይማኖት የጥንትና የጧት ወዳጅና አለኝታ የነበረችው ኢትዮጵያችን በሙስሊሙ አለም አይን
እንደ ደመኛ ጠላት እየታየች ጂሃድ የሚታወጅባት አገር ሆናለች።

በእንዲህ አይነቱ ቅልበሳ በሚጋብዘው ድንበር ዘለል ትርምስ ገብተው የሚዳከሩት በመንግስት ደረጃ የተቀመ
ጡ ፀረ ህዝቦች ብቻ አይደሉም። በኦጋዴን ጦርነት ማግስት እንዳየነው ከሆነ የሶማሊያ መንግስት ጦር ተሸንፎ አገር ለ
ቆ በመውጣቱ ብቻ ግጭቱ አላቆመም ነበር። በወረራው ወቅት ተፈጥረው የነበሩት ትብብሮች (አልያንሶች) በዛው በወ
ገናዊነታቸው ቀጥለው የቅርብና የሩቅ ባእዳን እንደ ምርጫቸውና ጥቅማቸው አንዱ በመንግስት ሌላው በተቃዋሚዎች
በኩል እየተሰለፉ ግጭቶች እንዲበራከቱና እንዲፋፋሙ አድርገዋል። መንግስት ተቃዋሚዎቹን ለመቋቋም ከእለት እለ
ት ለባእዳን የማደሩን ሂደት እያጎለበተ እንደሄደ ሁሉ ተቃዋሚ ሃይሎችም ለፀረ መንግስት ትግላቸው ድጋፍ ለመሰብሰ
ብ በሚያደርጉት ጥረት የህዝባችንን አጀንዳ አንግበው ህዝባችንን ይዘው ለግልፅ ህዝባዊና አገራዊ አላማ ከመታገል ይ
ልቅ ከሃገር ጥቅም፤ ክብርና ደህንነት ጋር ግንኙነት በሌላቸው አጀንዳዎች ከውጭ ሃይሎች ገጠሙ። በዚህም በአዳን
በውስጥ ጉዳያችን ገብተው የሚፈተፍቱበት ሰፊ በር እንደተከፈተ ትላንትም ያየነው ዛሬም እያየን ያለነው ክስተት ነው
።

ትላንት በየካቲት ማግስት የነወያኔ/ሸአብያ ከሞቃዲሾ፤ ካርቱምና ጀዳ ዛሬ ደግሞ ሌሎች ተቃዋሚዎች ከአስ
መራና ከሞቃዲሾ የተደረገውና የሚደረገው የተቃውሞ ትግል የዚህ 'ድንበር ዘለል' የቅልበሳ ማግስት ቀውስ አንድ የማ
ይናቅ ገፅታ ነው። በየካቲት ማግስት ተራማጅና አገር ወዳድ ሃይሎች የየካቲትን እሴቶች ይዘው ለመንቀሳቀስ ሲሞክሩ
''አብዮታችንን'' ሲሉ ከምእራቡ አለም፣ ''ብሄራዊ ነፃነታችንን'' ሲሉ ደግሞ ''ከሶሻሊስቱ ሰፈር'' እየተጋጩ ውጥንቅ
ጡ የወጣና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቀው ነበር። በዚህም የተነሳ ሚልዮኖች የቆሙለት የዴሞክራሲና የሃገር አንድነ
ት ጉዳይ እዚህ ግባ የሚባል አሰባሳቢ ሃይል አጥቶ ስመ ጥፉው የለንደን ጉባኤ እንደደረሰባቸውና ይቺን ''ባለቤት ያጣ
ች'' አገር ለወያኔ/ኢህአዴግ ለማስረከብ እንደተገደዱ ተመልክተናል። ዛሬም ቢሆን ከግንቦት ድሎችና እሴቶች ውጭ
በአንድ በኩል በፀረ ህዝቡ መንግስትና በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ድሎች ''ድሎቻችን'' በማይሉ ተቃዋሚዎች መካከ
ል ባእዳን ወገን ለይተው የሚያፋፍሟቸው ግጭቶች እየተበራከቱ ናቸው። በዚያው ልክ ደግሞ የሚልዮኖች ህልምና አ
ጀንዳ የሆነው የዴሞክራሲ፣ የሃገር ክብርና አንድነት አጀንዳ የረባ ባለቤት አጥቶ የሃገራችን እጣ ፈንታ እንደ ግንቦት 8
3 ከኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ብሎም ከኢትዮጵያ ህዝብ ይልቅ በዝግ ችሎት በጥቂቶች ሊወሰን የሚች
ልበት የዳግማዊ ለንደን አይነት አደጋ አፍጦና አግጦ ይታያል።

## ክፍል ሁለት - ምን አፀፋ?

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ስንሰሳ የሚቀርበው ጥያቄ ''ምን እናድርግ?'' የሚለው እንደሆነ ግልፅ ነው። መኢሶን በአ
ለም ካሉ ቀውሶችና ችግሮች ከተገቢ ድርሻዋ በላይ ለተሸከመችው ለዚች መከረኛ አገራችን ውስብስብ ችግሮች ''ይ

ኽ ነው'' ብሎ የሚሰነዝረው ቀላል መፍትሄ የለውም። ሆኖም ትላንት ካለፍንበትና ዛሬ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በእርግጠኛነት የሚላቸው ሁለት ነገሮች አሉ።

አንደኛ ከአስራ አራት አመታት ጀምሮ በአንድ በኩል በጎጠኝነት በሌላ በኩል ደግሞ በግሎባላይዜሽን ሁለት የጥፋት ፅንፎች ስትታመስ የቆየችው ሳያንሳት አሁን ደግሞ የግንቦት ማግስት ቀውስ የተጨመረባት ይቺ አገር ወደ ባሰ ጥፋት እየሄደች የየካቲት ቅልበሳ የጀመረውን ግንቦት ሊጨርስ የሚችልበት አስከፊ አዙሪት ውስጥ እየወደቀች እንደሆነ በግልፅ የምናየው ሃቅ ነው። ሁለተኛ ይህንን አስከፊ አደጋ ለመቋቋም የሚቻለው በአንድ ሁሉን አውቃለሁ በሚል ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ አማካኝነት ሳይሆን በጠቅላላው የዚች አገርና የዚህ ህዝብ እጣ ፈንታ ይመለከተናል በሚሉ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች የጋራ ትግል ብቻ እንደሆነ፣ ይህም እውን ሊሆን የሚችለው እነዚህ ሃይሎች በሙሉ መክረውና ዘክረው አንድ የጋራ ስትራቴጂ ሲነድፉና በአንድ የጋራ መድረክ ተሰባስበው ሁሉም በአንድ አቅጣጫ ሲገፋ ብቻ እንጂ እንደ የካቲቱ ማግስት አንዱ ወደ አራምባ ሌላው ወደ ቆቦ እያመላከተ በሚካሄድ ለፀረ ህዝቦች ብቻ በሚያመች ግርግር እንዳልሆነ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል።

በየካቲት ማግስት ህዝባችን የተቀማቸውን ድሎች መልሶ እጁ ለማስገባት ያደረገው ተጋድሎ የተሸነፈው በሸብር ብቻ አልነበረም። ''ሁሉም ለየካቲት ድሎች!'' ብሎ እነዚህን ድሎች ለማስመለስ ሚልዮኖችን ለማንቀሳቀስ የሚችል የተባበረ የዴሞክራሲያዊ ሃይሎች አመራር ስላልነበረም ነው። ሶስቱ ዋና ዋና የየካቲት ተዋንያን ህብረ ብሄር ድርጅቶች ማለትም - ኢዲዩ፣ ኢህአፓና መኢሶን - በራሱ በአብዮቱ ትግል ወቅት ተከፋፍለውና ጎራ ለይተው የሚፋለሙ ሃይሎች ነበሩ። በርእዮተ አለምም ሆነ በፖለቲካ ሌላው ቀርቶ በራሱ በአብዮቱ ግኝቶች ወይም ድሎች ጉዳይ በጣም የተለያዩና አንዳንዴም ተፃራሪ አቋሞች ነበሯቸው። ስለ ቅልበሳውም ምንነትና እውነታ ምንም አይነት የጋራ ግንዛቤ አልነበረም። በመሆኑም ከቅልበሳው አስር አመት በኋላ ኢዴሃቅን እስከመሰረቱበት ወቅት ድረስ በጋራ የትግል መድረክ ላይ መቆም የሚችሉ ሃይሎች አልነበሩም። የህብረ ብሄር ሃይሎች እንደዚህ ሆኖ የብሄር ድርጅቶች አቋም ደግሞ ምን እንደነበረ ከፍ ብለን ጠቁመናል።

ድሮውንም እነ ኢህአፓና ኢዲዩ የደርግ ሰላዮች ጉረና ብለው ይታገሏቸው የነበሩትን አብዮቱ ያፈራቸውን የህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስልጣን ተቋማት ደርግ ደግሞ በበኩሉ በመኢሶን ደጋፊነት ፈርጆ በአመፅ ሲያፈራርሳቸውና የገበሬ ማህበራት ተመራጮች ተሸረው፤ ታስረው፣ ተረሽነው፣ ተሰደው በገጠር ለገበሬው ሳይሆን በገበሬው ላይ በሚሰሩ ተሿሚዎች ተተኩ። በከተሞችም በነፃና በትርፍ ጊዜያቸው ለህብረተሰቡ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ የቀበሌ ተመራጭ ዜጎች እንደዚሁ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነው፣ ለእስር ተዳርገውና ተሰደው ቦታቸው ለለየላቸው ዱርየዎችና በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ተሰጠ። ጠግቦ ማደር ጀምሮ የነበረው ገበሬ መሬቱን ታቅፎ ራሱ እየተራበ ምርቱን በኮታ ስም ለመንግስት እህል ቦርድ እንዲያስረክብ ተገዶ ይህንን አሻፈረኝ ሲል ተመታ። ይህንን ሁሉ በወቅቱ በፀረ ደርግነት የተሰለፉ ተቃዋሚ ሃይሎች በሙሉ ''ቅልበሳ'' ብለው በስሙ አልጠሩትም ነበር። እርግጥ ድርጅታችን መኢሶንና አንዳንድ ሌሎች ተቃዋሚዎች በዘገየ ሰአትም ቢሆን ለሃገሪቱ ችግር ያለው አንድ መፍትሄ ' የሃገራችን ገበሬዎች በየመንደራቸው እንደገና የፖለቲካ ስልጣናቸውን እንዲጎናፀፉ፣ የመሬታቸው ብቻ ሳይሆን እንደገና የምርታቸው ባለቤት እንዲሆኑ'' ማድረግ ብቻ እንደሆነ ጠቁመው ይህንን ቅልበሳ ለመዋጋት ታግለዋል። ይህ ትግል ለምን አልተሳካም?

ስለ የካቲት ሽንፈት በተነሳ ቁጥር እንደ ዋና ምክንያት ሆኖ እስከዛሬ የሚወሳው ድክመት በፀረ ደርግ አቋም የተሰለፉ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች - በተለይም መኢሶንና ኢህአፓ - ተባብረው አለመታገላቸው ነው። በኛ ግምት ይህ የሽንፈቱ አንድ እንጂ ዋናው ምክንያት አልነበረም። የአብዮቱ ድሎች የተገኙት በየካቲት ማግስት በፀረ ደርግ ትግል የተሰማሩት ህብረ ብሄርና የብሄር ድርጅቶች የጋራ ግንባር ፈጥረው ባደረጉት ትግል አልነበረም። መሬትና መብት ብሎ የተነሳው የሚልዮኖች ትግል ለድል የበቃው በራሳቸው በደርግ መሪዎች ተሳትፎና ዘማቾች፤ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት ታጋዮች፤ መኢሶንና ሌሎች ተራማጅ ሃይሎች ይህንን ህዝባዊ ተጋድሎ ለማደራጀት፤ ለማስተባበርና ለመምራት ባደረጉት ከባድ መስዋእትነት በጠየቀ ጥረት እንደነበረ የታሪክ ሃቅ ነው። በመሆኑም የደርግ መሪዎች በክህደት ሌሎች ለየካቲት ድሎች የማይናቅ አስተዋፅኦ አድርገው የነበሩ እንደ ማሌሪድና የወዝአደር ሊግ የመሰሉ ድርጅቶች ደግሞ በአድርባይነት ጎዳና ሲሰማሩ ይህንን በበቂ ተከላክሎ ሃገራችንን ከጥፋት ማዳን ያልተቻለው እስከዚህም ድሮውኑ

ም ለድሉ በአንድነት ያልታገሉት ፀረ ደርግ ድርጅቶች ይህንን ድል ለማስመለስ የጋራ ትግል ባለማካሄዳቸው አልነበረም። የሽንፈታችን ዋና ምክንያት ሚልዮኖች ድላቸውን ያለመነጠቅ አጀንዳ አንግበው ለመንቀሳቀስ ዝግጁ በነበሩበት ሁኔታ እንደ መኢሶን ያሉት ከዚህ ህዝባዊ ድል "አለንበት" ይሉ የነበሩ ድርጅቶች ይህንን "የየካቲት ድሎች ይከበሩ" የሚል ህዝባዊ አጀንዳ በግልፅ አንግበው ከመዋደቅ ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶችና ድክመቶች ከሁሉም በላይ ደግሞ የቅልበሳውን ምንነትና አሳሳቢነት በወቅቱ መረዳት አቅቷቸውና የዳተኝነት አባዜ ተጠናውቷቸው የሚጠበቅባቸውን ግንባር ቀደም ሚና ባለመወጣታቸውም እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ዛሬም ከፊታችን የተደቀነው አደጋ ከዚህ ብዙም የሚለይ አይደለም። ባለንበት የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግንቦትንም እንደ የካቲት ባለቤትና አስመላሽ ያጣ ድል ሊሆን የሚችልበት አደጋ በግልፅ አለ። ትላንት ለሽንፈት ያበቃን ፀረ ደርግ ነን የሚሉ ሃይሎች መሰባሰብ አለመቻል ሳይሆን የየካቲትን ድሎች "የኛ" ብለው የሚቆጥሩ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች የህዝባችንን አጀንዳ በግልፅ አንግበው ባለመታገላቸው እንደነበረ ሁሉ ዛሬም ቢሆን ያለው ዋናው ችግር "ፀረ ወያኔ" ነን የሚሉና እጅግ የተሰበጣጠሩ አጀንዳዎች ያነገቡ ሃይሎች የአለመሰባሰብ ሳይሆን የግንቦት ድሎች ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ተሰባስበው እነዚህን ድሎች ለማስመለስና በነሱ ላይ ለመገንባት የሚያስፈልገው ጥራትና ቁርጠኝነት ያለመኖሩ ችግር ይመስለናል። እነዚህ ወገኖቻችን በየካቲት ማግስት መኢሶንን ተጠናውቶት በነበረው አይነት የውዥንብርና የአደገኛ ዳተኝነት አባዜ ተጠናውቷቸው ወርቅማ ጊዜ ሲያባክኑ እየታዘብን ነው።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ካለንበት ቀውስ ለመውጣት ብዙም አማራጮች እንደሌሉን እናያለን። በትግል አጀንዳችን ግንቦት ያፀደቃቸውን የሰላም፣ የበጎ ለውጥ፣ የዴሞክራሲ፣ የህዝቦች ወንድማማችነት፣ የሃገር አንድነትና ብልፅግና እሴቶች አጉልተን ማንገብና ኢትዮጵያችን ባለቤት ያጣች አገር እንዳትሆን በነሱ ዙሪያ በቁርጠኝነት መሰባሰብ ያስፈልጋል። የትግል ስትራቴጂያችን የሚልዮኖችን ድል ለማስመለስ የግድ ሚልዮኖችን ማንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ አምኖ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ህዝባችንን በቅልበሳው የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ መዘዞች ዙሪያ ትግሉን እንዲያፋፍም መቀስቀስ ይኖርብናል። ለህዝባችን በዚህ መልክ የምናደርገው የትግል ጥሪ አድማጭ እንዲያገኝ ደግሞ ተአማኒነትን መልሶ የገነባና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ ህዝባዊ አመራር ያስፈልገናል። ባጭሩ አሁን ካለው አደገኛ ውዥንብር ባሻገር " ለህዝባዊ አጀንዳ፤ ህዝባዊ ትግል፤ ተአማኒ አመራር" ብለን በምናጠቃልለው ስትራቴጂ ዙሪያ ተሰባስበን መዋደቅ ይኖርብናል ብለን ስለምናምን የዚህን ህዝባዊና አገራዊ ስትራቴጂ ይዘትና ለቀጣዩ ትግል ጥራት ስንል በመነዛት ላይ ካለው ውዥንብር ጋር እያነጻጸርን በአጭር በአጭሩ ለውይይት ለማቅረብ እንሞክራለን።

## 1/ ለህዝባዊ አጀንዳ

ህዝባዊ አጀንዳ ለምንለው ቀላሉ ትርጉም ይህንን ህዝባችን የተሰዋለትን "የድምፄ ይከበር" አጀንዳ ያለአንዳች ማወላወል እኛም መልሰን እንደሱ ማንገብ ይኖርብናል ማለት ነው። "በህዝባዊ አጀንዳ" የሚለውን ዛሬ የተያዘውን ተጋድሎ ይዘት የምናጠቃልለው በአንድ ህዝባዊ ትግል ሂደት "የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በነሱ ላይ መገንባት" በሚለው ግልፅና ቀላል መፈክር ነው።

የግንቦትን ድሎች ማስመለስ ስንል ምን ማለታችን ነው? የግንቦትን ድል እናስመልስ ማለት የዛሬ ሶስት አመት ምርጫው ተጭበርብሯልና የህዝቡ ድምፅ እንደገና ይቆጠር ማለት አይደለም። ሌላው ቢቀር በወቅቱ የነበሩት ማስረጃዎች በኢህአዴግ ምርጫ ቦርድ ተዘርፈው ከጥቅም ውጭ በመሆናቸውና በሌሎች በርካታ ምክንያቶች የተነሳ ይህ አይነቱ አካሄድ የሚያዋጣ አይሆንም። የግንቦት ድሎችን ማስመለስ ሲባል ከዚህ ይልቅ ከአጭር ጊዜ አንፃር ሲታይ ከግንቦት በፊት በፕሬስ ነፃነትም ሆነ በመደራጀት መብት፣ በመሰብሰብም ሆነ በሰላማዊ ሰልፍ መጥራትና መውጣት መስከ የነበሩት ከዝቅተኛም ዝቅተኛ የሚባሉ ዴሞክራሲያዊና መሰረታዊ መብቶች ተመልሰው እውን እንዲሆኑ፣ በግንቦት ሳቢያ የታሰሩ ዜጎች በሙሉ እንዲፈቱ፣ በግፍ በተገደሉት ዜጎች ጉዳይ ተጠያቂነት እንዲኖር ወዘተ ትግሉ ተፋፍሞ ይቀጥል ማለት ነው። ነገር ግን የግንቦት ድሎችን ማስመለስ ሲባል ለነዚህ መሰረታዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገው ት

ግል ከሰፋፊና ዘላቂ አጀንዳዎች ጋር እንዲቆራኝና የግንቦት ድሎች እንዲከበሩ በሚል የሚንቀሳቀሰው ትግል በዚያው ሂደት ለዴሞክራሲ መሰፈንና ይህም በነፃ ምርጫ አማካኝነት እንዲቋጠር መታገልንም የግድ ይጨምራል። የድሎች ማ ስመለሱ ትግል በዚህ መልክ "በግንቦት ድሎች ላይ መገንባት" ከሚለው ቀጣይ ህዝባዊ አጀንዳ ተለይቶ እንዳይታይ የ ሚያስገድዱ ብዙ ምክንያቶች አሉ።

አንደኛ ፀረ ዴሞክራሲነትንና ሽብርን እንደ ህልውናቸው ዋስትና አድርገው ከሚቆጥሩ የኢህአዴግ መሪዎች ከ እንግዲህ ያለ ህዝባዊ ተጋድሎ እነዚህን መብቶች መልሶ መጎናፀፍ አይቻልም እንጂ የታሰሩት ሁሉ ቢፈቱና በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበሩት የመደራጀት፤ የፕሬስ ወዘተ መብቶች ተመለሱ ቢባሉ እንኳን የኢህአዴግ መንግስት እስከ ቀጠለ ድረስ ተመልሰው ላለመነጠቃቸው ምንም ዋስትና አይኖርም። የሚፈቱ የፖለቲካ መሪዎች ሆኑ ሌሎች ታጋዮች ህዝባ ችንን ይዘን ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ትግል እናካሂዳለን ካሉ መልሰው ይታሰራሉ። የነፃው ፕሬስ ባልደረቦች እንደ ገና እንደ ቅድመ ግንቦቱ 'የህዝብ ድምፅ" እንሆናለን ካሉ እነሱም መልሰው ለእስር ይዳረጋሉ ወይም ይዘጋሉ።

ሁለተኛ እነዚህ የመደራጀት፤ የፕሬስ ወዘተ መብቶች በቀድሞ ግንቦቱ ወቅት በነበሩበት "አላስተማማኝ" ደረ ጃ እንኳን እውን ሊሆኑ የሚችሉት በነዚህ ዙሪያ የሚደረገው ህዝባዊ ትግል አይሎ የኢህአዴግ መሪዎች የያዙትን የጥ ፋት ሂደት እንዲቀይሩ ለማስገደድ የሚችልበት ደረጃ ሲደርስ ብቻ ነው። ትግላችን አይሎ እዚህ ደረጃ ከደረሰ ደግሞ ከወዲሁ በፖለቲካው መድረክ መሰረታዊ የሆነ የሃይል ሚዛን ለውጥ ተከስቶ የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የሚፈግፈግ እ ኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና ህዝባችን ደግሞ የማጥቃትና የድል በጎ አዙሪት ውስጥ የምንገባበት ሁኔታ ተመቻችቷል ማለት ነው። በመሆኑም በዚህ አዲስ በተፈጠረ አምርታ ትግሉ ቀጥሎ በዴሞክራሲ መስፈን መቋጠር የሚቻልበት ሁኔ ታ እያለ ተገኙ በተባሉት ዞሮ ዞሮ ገና በቋፍ ያሉ ድሎች ተዘናግቶ ህብረተሰቡ ትግሉን ጋብ ካደረገ የኢህአዴግ መሪዎ ች እነዚህን ሁሉ "በመጀመሪያው አጋጣሚ" ተጠቅመው መልሰው ሊነጥቁ የሚችሉበት ፋታ የመስጠት ያህል አደገኛ አካሄድ ይሆናል። ኢዴሃህ በዚህ ጉዳይና ማስመለስና መገንባት በሚለው ጥያቄ ትስስር ለዩትራክት ስብሰባ ባሰናዳው ሰነ ድ ላይ ሲያትት፤

"በህብረታችን እምነት ዛሬ የዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ሃይሎች ዋናና አንገብጋቢ ተግባር የኢህአዴግ መሪዎች በዚህ መልክ ለማዝረክረክና ለማውደም የሚሞክሯቸውን እነዚህን የህብረተሰባችንን ድሎች በህዝባዊ ትግል አስመልሶ መንከባከብና በነሱ ላይ እየገነቡ ወደ ፊት የመራመድ አደራ ነው። ማስመለስ፤ መንከባከብ፤ በነሱ ላይ መገንባት። ዛሬ ባለንበት የሽብር አገዛዝ ስር ሶስቱ አላማዎች በአንድ የህዝባዊ ተጋድሎ ሂደት የሚረጋገጡ እንጂ ተነጣጥለው የሚታ ዩበት ምንም ተአምር አይኖርም። መሪዎቻችንንና ሌሎች በሽህ የሚቆጠሩ ታጋዮችን ከእስር ማስፈታት፤ የነፃው ፕሬስ ባልደረቦች በሙሉ ተለቀው የህዝብ ድምፅነት ሚናቸውን እንዲቀጥሉ መሟገት፤ በህዝባችን ላይ ለተፈፀሙ ግፎች ሁ ሉ ተጠያቂነትን መጠየቅ፤ የህዝቡን ድሎች ለማስመለስ የሚካሄዱ ተጋድሎዎች ናቸው። ነገር ግን በዚሁ የትግል ሂደ ት ገፍተን ዴሞክራሲ፤ የህግ የበላይነት፤ ተጠያቂነት በሚሰፍኑበት በህዝባዊ ስርአት ካልቋጠርናቸው የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት እስካለ ድረስ ነገሩ ሁሉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆናል። ተመልሰው ይነጠቃሉ። ባጭሩ ለማስቀመጥ ድሎቻ ችንን አስመልሰን ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ስርአት ለሚደረገው ሂደት ሳያቋርጡ መታገል ጊዜው የሚጠይቀው ታ ሪካዊ ሃላፊነት ነው።" በማለት ጊዜያዊና ዘላቂ አላማዎች እንዴት የተሳሰሩ እንደሆኑ ለመጠቆም ሞክሯል።

እዚህ ላይ እንግዲህ ለቀጣዩ ትግል ጥራት ሲባል አንድ መነሳትና መመለስ ያለበት ጥያቄ ያለ ይመስለናል። የግ ንቦት ምርጫ በተከተሉት ወራት ይህ የህዝብ ድምፅ ይከበር የሚለው ጥያቄ "የግንቦት ሃይሎች" ብለን ልንጠራቸው የ ምንችለው የሃገራችን ዴሞክራቶች ከህዝባችን ጎን ተሰልፈው ዳር እስከዳር ያነገቡት መፈክር ነበር። ዛሬ ወደ ተከላካ ይነት ወርደን በየወቅቱ እኛ አውጥተን አውርደን ለህዝባችን ያዋጣል በምንለው ሳይሆን የኢህአዴግ መሪዎች በየጊዜው በሚያስጨብጡን አጀንዳዎች ላይ ታች እያልን እንገኛለን። በግንቦት ድሎች አጀንዳ ዙሪያ የተደረገው ትግል ያ ሁ ሉ መስዋእትነት ከተከፈለ በኋላ የተጠበቀውን ፍሬ ስላልሰጠ "ይህ መፈክር ጊዜው አላለፈበትም ወይ?" የሚሉ ጥያቄዎ ች እየተበራከቱ ይታያል። ከዚህም አልፎ ተርፎ ይህንን ጉዳይ "ሞኝ የያዘው ፈሊጥ" አድርጎ በመቁጠር ለማጣጣል የ ሚሞክሩ ሃይሎች እየታዘብን ነው።

ከዚህ አንፃር በጣም አሳሳቢ የሚመስለን በጉዳዩ ላይ ምንም የረባ ክርክር ሲደረግ አለመስተዋሉ ነው። ሆኖም በፅሁፍ ተብራርቶ የቀረበ ነገር ባይኖርም በተለይ በውጭ ካሉ የቅንጅት መሪዎች አካባቢ አንዳንዶቹ በየፓል ቶኩና ቴ ሌኮንፈራንሱ ከሚሰተጋቡት አንዳንድ አስተያየቶች ስንነሳ የግንቦት ድሎችን የማስመለሱ አጀንዳ እየተድበሰበሰ መሆኑ ን እናያለን። በአንድ ፓልቶክ ላይ ከቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ይህንን መፈክር "ተጨባጭነ ት የሌለው" (ቬግ ስሎጋን) ብለው ሲፈርጁት ተደምጠዋል። በዚሁ መንፈስ ከዚሁ ከቅንጅቱ አለም አቀፍ አመራር አቶ ብርሃነ መዋ በአንድ በቴሌኮንፌራንስና በፓልቶክ የግንቦት ነገር ከምርጫው ጋር አልፏል፤ ብዙ ድርጅቶች በተለይ በ ውጭ ያሉት አልተሳተፉበትም፤ ያንን ጥያቄ አሁን ከማንሳት ይልቅ በቅንጅቱ ስምንት ነጥቦች በመመርኮዝ ዴሞክራሲ ያዊ ተቋማትን ለመጠናከር በብሄራዊ እርቅና በድርድር ጎዳና መሰማራት ያስፈልጋል የሚል አቋም ሲያስተጋቡ ተደም ጠዋል። የቅንጅቱ ስምንት ነጥቦችና የተቋማት ግንባታ ጥያቄዎች ጨርሶ የማያጣሉ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ አላማዎች ናቸው። ለግንቦት ድሎች እንታገል ስንል እነዚህንም መፈክሮች ያነገብን መሆኑ በጣም ግልፅ ነው። ነገር ግን የግንቦት ን ጉዳይ ሳያነሱ ለነዚህ እንታገላለን ማለት በርካታ ችግሮች አሉበት።

የዳኝነት ነፃነት፣ የህግ የበላይነት፣ ነፃ ምርጫ ወዘተ የሚሉት መፈክሮቻችን በአለፉት 15 አመታት ከኢህአዴ ግ መሪዎች ጋር ስንከራከርባቸው ብቻ ሳይሆን "ስንዳረቅባቸውና" ከሞላ ጎደል የደንቆሮ ጨዋታ ስናካሂድ የቆየንባቸው መፈክሮች ናቸው። በነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ላይ ትግላችንን የአህያ ውድቂያ እያደረገ ሲያስቸግረን የቆየው እነ አቶ መለስ የደርግን እምባገነን አገዛዝ ጥለን ዛሬ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት መስርተናል፣ በሃገራች ን የህግ የበላይነት አስፍነናል፣ የዳኝነት ነፃነት አረጋግጠናል ወዘተ እያሉ ሲመፃደቁ መቆየታቸው እንደሆነ እናውቀዋለን ። በዚሁ ልፈፋቸውም በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት ተቀባይነት አግኝተው ይኸው ኮሙኒቲ በነአቶ መለስ ስታሊናዊ ህገ መንግስት አማካኝነት "በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ዘር ተዘራ" እስከ ማለት ዘልቆ፤ መድበለ ፓርቲ ስርአት ተመሰረተ ብ ሎ አሞግሶ፣ ሲካሄዱ የነበሩትን ምርጫዎች "ዴሞክራሲያዊ" እያለ ሰይሞና ይህንን ሁሉ "ጠቅለል አድርጎ" በማቅረብ እነ አቶ መለስን "አዲስ የዴሞክራሲያዊ መሪዎች ትውልድ" ብሎ ሲያሞካሽ እንደ ነበረ እናውቃለን።

በአጭሩ ባለፉት አስራ አምስት አመታት እነዚህን ዴሞክራሲያዊ እሴቶች አንግበን ስንኳትን አንዳንድ የማይና ቁ ድሎች ብናስመዘግብም ከኢህአዴግ መሪዎች አንፃር የማያወላዳ የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ የበላይነት እንዳልነበረን ና ይህ ደግሞ በተራው ትግሉን አስቸጋሪ አድርጎት ከአለምነው ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዳንደርስ እንዳደረገን ሊካድ የሚችል ጉዳይ አይደለም። ከግንቦቱ ምርጫ ሁለት አመት ቀደም ብሎ በሃምሌ 1995 አ.ም. መኢሶን ለኢዴሃህ ምስረታ ጉባኤ ባቀረበው ሰነድ ላይ እነዚህ ሰፋፊ የሆኑ አገራዊ ራእዮችና መፈክሮች ብቻቸውን ለምን ለህዝባዊ ድል ወሳኝ የ ሆነውን የፖለቲካ የበላይነት ሊያስጨብጡን እንዳልቻሉ ሲተች

" ዴሞክራሲ አልን ነፃ ምርጫ፤ ሰብአዊ መብቶች አልን የህግ የበላይነት፤ መድበለ ፓርቲ ስርአት አልን የሃገ ራችን አንድነት የነዚህ ጥሪዎች ችግራቸው ወያኔ እኔም አምንባቸዋለሁ ማለቱ ብቻ አይደለም። ከተቃዋሚዎች ይልቅ እኔ በተግባር እያዋልኳቸው ነው ባይም ነው። ....... ትልቁ ልብ ያላልነው (ወይም መቀበል ያልቻልነው) ሃቅ ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ ትግል በመፋለም ላይ ያለነው ሁለት አናሳ ሃይሎች ነን። በአንድ በኩል ወያኔና ካድሬዎቹ። በሌ ላ በኩል ተደራጅቶ ለመታገል የሚሞክረው የነቃ አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሃይል። በዚህ ትግል እነዚህ ሁለት አና ሳ ሃይሎች ያሏቸው የትግል ምርኩዞች የተለያዩ ናቸው። አናሳው ወያኔ የመንግስት የፋይናንስ አቅም አለው። የመንግስ ት የመረጃ መረብ፤ የፖሊስና የጦር ሰራዊት አለው። በዚህ ተመርኩዞ በሃገር ደረጃ ያንሰራራና በህዝብ ላይ የተጫነ የ ካድሬዎች መዋቅርና ሰራዊት አለው። ከህዝቡ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነውን ገበሬ በመሬት ስሪቱ አስሮ ይዞታል። ዲፕሎማሲያዊ ምርኩዝ አለው።

" አናሳዎቹ እኛ ከነዚህ ውስጥ ማንኛቸውም የሉንም። ይህንን ድክመታችንን ካልተወጣን፣ ከወያኔዎቹ ይበልጥ ጠንክረን ካልተገኘንና በህብረተሰባችን ውስጥ ዛሬ በማያወላዳ ሁኔታ ለአፋኙ አገዛዝ የሚያደላውን የሃይል ሚዛን ካል ቀየርን እንኳን የሚቀጥለው ቀርቶ እስከ ወዲያኛውም ቢሆን ምርጫ ተሳትፈን አሸንፈን በሃገራችን ዴሞክራሲ አናሰፍን ም። እኛ አናሳዎቹ በአናሳው ኢህአዴግ ላይ የበላይነት የማግኘታችን ተስፋ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም በሚያ ራምደው ፖለቲካ ምክንያት ፈፅሞ ሊደርስበት የማይችለውን በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን

ማስለፍ ብቻ ነው። ዛሬ ያለን የሞራል የበላይነት፤ ዛሬ ያለን የሃገር ፍቅርና የዴሞክራሲያዊነት የበላይነት በፀረ ህዝቡ ና በፀረ ዴሞክራሲው ወያኔ ላይ ተጨባጭ የፖለቲካ ትርጉም የሚኖረው በዚህ መልክ ህዝባችንን ከጎናችን አሰልፈን ስ ንፋለመው ብቻ ነው። **መራራውን ሃቅ እንቀበል ካልን ዛሬ ይህንን የሞራልና የሃገር ፍቅር የበላይነት በፖለቲካ የበላይነ ት መመንዘር እንዳልቻልን ግልፅ ነው።**" (ሰርዝ የተጨመረ)

በዚሁ ሰነዳችን ላይ "ከሂደቱ እንጂ ከውጤቱ ምንም ሳንጠብቅ" እንገባበት ያልነው የግንቦት ምርጫ እንደፈ ለግነውና እንደጠበቅነው ይኸንን ሁሉ ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ ቀይሮታል። ግንቦት ባይቀለበስ ኖሮ የዴሞክራሲ፣ የህግ የ በላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት....ድል ነበር። ግንቦት እነዚህን ሁሉ እሴቶች "ተጨባጭ" ያደረገና ማን በልፊፋ ደረጃ ማን በሃቅ ለነዚህ እንደቆመ ግልጥልጥ አድርጎ ያሳየ ሂደት ነበር። ግንቦት በአንድ ሂደት በነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ላይ የሃገራ ችን ዴሞክራቶች በውስጥም በአለም አቀፍ ደረጃም ወደ አጥቂነት የኢህአዴግ መሪዎች ደግሞ በአስራ አምስት አመቱ **የአገዛዝ ዘመናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ** ወደ ተከላካይነት የወረዱበት ሂደት ነበር። የተመዘገበው ተጨባጭ ድል ስለነበ ረ እነ አቶ መለስ እንደ ቅድመ ግንቦቱ ሁኔታ በአፈ ጮሌነት ብቻ "ዴሞክራቶች ነን" ብለው ለማወናበድ እንደማይች ሉ ተረድተውና የሚይዙት የሚለቁት አጥተው የሸብር ጎዳና እንዲመርጡና በዚህም በእውነተኛ ገፅታቸው እንዲጋለጡ የተገደዱበት ሂደት ነበር። ሴት ተቀን የሚያልሙትም እኛም ህዝባችንም የግንቦትን ነገር ረስተን፤ "በተጨባጭነት" ስ ም ከተጨባጭም ተጨባጭ የሆነውን ግንቦት ያጎናፀፈንን የፖለቲካ የበላይነት የትም በትነን "የህግ የበላይነት" "የዳኝነ ት ነፃነት" "ቀጣይ ነፃ ምርጫ" ..... እያልን በሰዶ ማሳደድ አካሄድ ወደ ቅድመ ግንቦቱ የተንሳፈፈ ትግላችን እንድንዘፈ ቅላቸው ነው።

ዛሬ የሃገራችንን ዴሞክራቶች ፀረ ኢህአዴግ ትግል በማዝረክረክና በማዳከም ላይ ያለው ዋና ምክንያት በዚህ " ለምን አጀንዳ እንታገል?" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ያለው ውዥንብር ይመስለናል። ይህንን አደገኛ ውዥንብር ለማጥራት ከተፈለገ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ከማንኛውም በፀረ ኢህአዴጉ ትግል አለሁበት ከሚል ድር ጅት ወይም መሪ " በምን አጀንዳ?" የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ አቅርበው ለዚህ ግልፅ መልስ ለማግኘት መጣር ይኖርባቸዋ ል እንላለን። ከዚህ ተያይዞ ደግሞ ይህንን ህዝባዊ አጀንዳ አንግበናል የሚሉ ሃይሎች "እንዴት እንታገል?" ለሚለው ጥ ያቄ ግልፅ የሆነ መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ደግሞ ወደ ሁለተኛው የህዝባዊ ስትራቴጂያችን ዘርፍ ያመጣናል ።

## 2/ ህዝባዊ የትግል ማእበል

በዚህ ጉዳይ ወደ ዝርዝር ነጥቦች ከመግባታችን በፊት "የትግል ስልት" በሚባለው ጥያቄ እየተከሰተ ስላለው ልዩነት አንዳንድ ነጥቦችን እንጠቁም። ልብ ብሎ ለሚታዘብ ሰው የሚያስገርም ቢሆንም በዚህ በትግል አጀንዳ ጉዳይ ጥርት ያለ የጋራ አቋም መያዝ ለትግላችን እንደ ህይወት እስትንፋስ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ይህ ወደ ጎን ተትቶ ዛሬ በመካ ሄድ ላይ ያለው ክርክር "ለምን እንታገል?" በሚለው ቁልፍና ተቀዳሚ ጥያቄ ላይ ሳይሆን "እንዴት እንታገል?" በሚለ ው ጥያቄ ዙሪያ የሚደረግ "ጋሪውን ከፈረስ የሚያስቀድም" እጉል ንትርክ ነው። ለምን "እጉል ንትርክ"? ለዚህ ሁለት ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ። አንደኛ ለግንቦት ህዝባዊ አጀንዳ እንታገል በሚለው ጉዳይ ከወዲሁ ስምምነት ካልተደረ ሰና ሁሉም የገዛ አጀንዳውን እያነገበ "ወያኔን ለመጣል" በምትል ቀጭን መፈክር እታገላለሁ የሚል ከሆነ የተመረጠው የትግል ስልት ቢመረጥ ለሃገራችን ምንም የሚያመጣው በጎ ነገር አይኖርም። ሁለተኛ የግንቦት ድሎች የሚልዮኖች ህ ዝባዊ ድሎች ናቸውና እነሱን አስመልሶ በነሱ ላይ መገንባት በሚለው ላይ ስምምነት ከተደረሰ ደግሞ ዋናው የትግል ስ ልት የድሉ ባለቤት የሆኑትን ሚልዮኖች መልሶ የትግሉ ወሳኝ ሃይል የማድረግ ስትራቴጂ መከተል ቢሆንም ይህንን ህዝ ባዊ የትግል ጎዳና ለመተካት እስካልተሞከረ ድረስ ሁሉም በመሰለው ትግሉን አግዛለሁ ቢል የስልት ጉዳይ ጨርሶ የሚ ያንተርክ መሆን የለበትም። ለምን?

ዛሬ በሃገራችን አላማውን ለማራመድ ከአመፅ፣ ከሽብርና ከህገ ወጥነት የትግል ስልት ሌላ ምንም አማራጭ የ ሌለው አንድ ሃይል ቢኖር ኢህአዴግ ብቻ ነው። የዚያኑ ያህል ደግሞ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ለአንድ አላ

ማና በአንድ አቅጣጫ ለመግፋት እስከተስማሙ ድረስ የትግል ስልት ምርጫቸው ወሰን የሌለው ሆኖ እናያለን። በዚህም የተነሳ ህዝባዊ አጀንዳ ያነገቡ ሃይሎች እናምንበታለን በሚሉት ህጋዊ ሆነ ህገ ወጥ፣ ይፋ ሆነ ህቡእ፣ ሰላማዊ ሆነ የት ጥቅ ትግል ሊሰማሩ የማይችሉበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ይህንን ካልን ዘንዳ ህዝባዊ ትግል ሰንል ምን ማለታች ን እንደሆነና ከዚህም አንፃር ያሉትን አሳሳች አቅጣጫዎች ምንነት ለመጠቆም እንደዚሁም ይህንን ህዝባዊ ትግል ለማነ ሳሳትና ሚልዮኖችን መልሶ የትግሉ ማእከል ለማድረግ ምን አካሄድ መከተል እንዳለብን ለመጠቆም እንሞክር።

ህዝባዊ የትግል ማእበል ሰንል ምን ለማለት ነው? ህዝባዊ የትግል ማእበል ሰንል ያለው መሰረታዊ ትርጉም አን ድ ነው። ግንቦት ላይ የትግሉ ማእከልና ዋና ሞተር የነበሩትን ሚልዮኖች ተመልሰው የትግሉ ባለቤት ለማድረግ እንስራ ማለት ነው። "ተመልሰው" የሚለው አባባል እንዲገባን ግንቦት እንዴት ሚልዮኖችን የትግሉ ዋና ተዋንያን ያደረገ ሂደ ት እንደነበረ መገንዘብ ይኖርብናል።

በግንቦት ምርጫ ሳቢያ የኢትዮጵያ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ድምፁን በመስጠት ያሳየው ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ያለውን ጉጉትና ጥማት ብቻ አይደለም። እያንዳንዱ ዜጋ ራሱን የትግሉ ባለቤት አድርጎ በመቁጠር አስርም አስራ አም ስትም ሰአት ሰልፍ ቆሞ ድምፁን በመስጠት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ብቁና ዝግጁ መሆኑን፤ ለዚህም እውንነት ለመዋደ ቅና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የሚጠየቀውን ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈልም ያለውን ቁርጠኛነት ያስመሰከረ በት ታሪካዊ ሂደት ነው። ይህንን ብቃትና ቁርጠኛነት በቅጡ ለመረዳት የግንቦትን ከድምፅ ብልጫ አልፎ የሚሄደውን ሌላ የድል ገፅታ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል።

ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የግንቦት ተጨባጭና የማይናቁ ድሎች የተገኙት በትግልና በመስዋእትነት ቢሆኑ ም በቅድመ ግንቦቱ ወቅት ህዝባችን በምርጫው በገፍ እንዲሳተፍና ያሻውን እንዲመርጥ የሚገፋፉት ሶስት "አጋዥ" ክስተቶች ነበሩ። የኢህአዴግ መንግስት ራሱ "እንከን የለሽ ነፃ ምርጫ ይካሄዳል፤ ያሻህን ምረጥ" ከማለት አልፎ በ ሚልዮኖች ፊት ለህዝብ ድምፅ በሬድዮና በቴሌቪዥን ሲፎካከር መታየቱ ለህዝቡ ምርጫ መሳተፍ ትልቅ አወንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው። ሁለተኛ ተቃዋሚ ሃይሎችም "በምርጫው ተሳተፍ፤ ትግሉን ቀጥል፤ የኢህአዴግ መንግስት አጭበ ርብሮ አሸንፋለሁ ካለ ድልህን ለማስመለስ ለምታደርገው ትግል የሚመጥን አመራር እንሰጥሃለን" በሚል ቅስቀሳ መሰ ማራቻው በምርጫ ጉዳይ ቀደም ሲል ህዝቡ ያሳየው የነበረውን ጥርጣሬ ወይም ስኬፕቲሲዝም ለማስወገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ሶስተኛ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ምርጫው የአለም አቀፍ መስፈርቶችን በሚያሟላ ሁኔታ እንዲካሄ ድ፤ ምንም አይነት ማጭበርበር እንዳይኖር ከዚህ በፊት ባልታየ ብዛት ታዛቢዎች መላኩ ህዝቡ በገፍ ወጥቶ ያሻውን እንዲመርጥ የገፋፋው መሆኑ የሚካድ አይደለም። ባጭሩ ህዝባችን እየሞተም፤ እየተሰዋም ቢሆን ያገኛቸው እነዚህ ድሎች ከሞላ ጎደል አመቺ በሆኑ ሁኔታዎች ታግዞ እንደሆነ ግልፅ ነው።

ነገር ግን በግንቦት ማግስት እነዚህ ሶስት አመቺ ሁኔታዎች ከሰሙ። ኢህአዴግ ነፃ ምርጫ የሚለውን ልፈፋ ት ቶ የህዝብ ድል ነጥቆ በለየለት ሸብር ተሰማራ። ተቃዋሚ ሃይሎችም በተለያዩ ምክንያቶች ቃል በገቡት መሰረት የህዝ ቡን ድምፅ ለማስከበር የሚደረገውን ትግል የማስተባበሩና የመምራቱ ነገር አልተሳካላቸውም። አለም አቀፉም ኮሙኒቲ "ምርጫው ተጭበርብሯል፤ ከአለም አቀፍ መስፈርቶችም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ጥማትና ብቃት ጋር በሚመጥን መልክ አልተካሄደም" ካለ በኋላ የሚካሄደውን ጭፍጨፋ ከአንገት በላይ እያወገዘ መልሶ ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር መዳራት ጀመረ። ህዝባችን ግን በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበሩ አጋዥ ሁኔታዎች በዚህ መልክ ከከሰሙ በኋላም "አምናቸዋለሁ" ያላቸው የፖለቲካ መሪዎች "ትግሉን ለኛና ለፈረንጆቹ ተወው" ብለው ድርድር በሚሉ መመ ሳጠር ስም ከመድረኩ እስኪያገሉት ድረስ በቆራጥነት እየተሰዋ ድምፄ ይከበር በሚል አጀንዳው ትግሉን ለወራት ቀጠ ሎ ነበር። ዛሬ ትግሉ ቢፈዝና ግራ ቢጋባ ህዝባችን ሳይሆን እኛ ይህንን አጀንዳ አንግበን ታግለን ለማታገል ብቃቱ ስላነሰ ን ብቻ ነው።

ህዝባዊ የትግል ማእበል ብለን ህዝባችን በግንቦት እንቅስቃሴ የትግሉ ማእከል ስለነበረ አሁን ያንንን ቦታውን መልሰን እናስጨብጠው ማለታችን ባለፈው ላይ በማተኮር "ደጉን ዘመን" የሚናፍቅ ወይም "የኖስታልጂያ" አካሄድ አ ይደለም። ትላንት የትግሉና የድሉ ባለቤት የነበረው ህዝባችን ዛሬ ደግሞ ከማንኛችንም ይበልጥ የቅልበሳውን ገፈት እየ

ቀመስ መሆኑን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል። እርግጥ በህይወት፣ በእስራት፣ በስደትና በእንግልት መስዋእትነት የከፈሉ ና በመክፈል ላይ ያሉ በደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ ታጋይ ወገኖቻችን አሉ። ከዚህ ክቡር መስዋእትነት በተጓዳኝ ህዝባችን በቅልበሳው አይቀሬ የሆኑና ነገ ደግሞ በሚባባሱ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች እየተቀጣና መቆሚያ መቀመጫ እያጣ መሆኑ መሰመር ይኖርበታል። ለኛ የመብት፣ የዴሞክራሲ፣ የተቋማት ግንባታ ወዘተ የሆነው ጥያቄ የድሉ ዋና ባለቤትና የቅልበሳው ዋና ሰለባ ለሆነው ለህዝባችን ደግሞ ከእለት እለት የህልውናና "የሞት ሽረት" ጥያቄ እየሆነ መሄዱን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ይህንን ሃቅ በቅጡ መጨበጥ አስፈላጊ የሚሆነው ነገሩ ሁሉ "ፍ የል በዚህ ቅምዝምዝ በዚያ" እንደተባለው እንዳይሆን "ህዝባዊ የትግል ማእበል እንዴት?" ለሚለው ጥያቄ ተገቢ መ ልስ ለመስጠት ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤ መነሳት የግድ ስለሚል ነው።

ህዝባዊ የትግል ማእበል እንዴት? ከሁሉ በፊት መሰመር ያለበት ጉዳይ ከፍ ብለን እንደጠቆምነው እንዲህ አይ ነቱ ትግል ምን በጎና ህዝባዊ ቢሆኑ በራእይና በስትራቴጂያዊ አላማዎች ዙሪያ ብቻ መቀስቀስ አለመቻሉ ነው። ይህ የህ ዝባችን ትግል የምርጫን ወቅት ሳይጠብቅ፣ ሰፋፊ ራእዮችን ወደ ጎን ሳይተው በተጨባጭ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትግ ሎች ዙሪያ መቀስቀስ ይኖርበታል የሚለውን አቋማችንን ከግንቦት ምርጫ በፊት ከነበረው ሁኔታ አንፃር ሲተች የመኢ ሶን ሰነድ የሚከተለውን አስፍሮ እናገኛለን፣

"ያለፉት አስራ አንድ አመታት የትግል ጉዞ ያሳየን አንድ ነገር ቢኖር በአነገብናቸው ክቡር ስትራቴጂያዊ መፈ ክሮች አማካኝነት ብቻ ህዝባችንን በሚልዮን እየቆጠርን አንቀሳቅሰን በሃገሪቱ ያለውን የሃይል ሚዛን መቀየር አለመቻላ ችንን ነው። እርግጥ ነፃ ምርጫ በተባለው የወያኔ ግርግር ተገቢ ተሳትፎ አድርገናል። ውጤቱ ምን እንደሆነ ከወዲሁ እ የታወቀ ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ አጋጣሚውን ተጠቅመን ተዋድቀናል። በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በእርግጥም የኢትዮጵያ ህዝ ብ በሚልዮን እየተቆጠረ ታሪካዊና አኩሪ ተሳትፎ አድርጓል። ግን የምርጫ ትግል በየአምስት አመቱ በሚከሰት ተሳትፎ የሚወሰን ትግል ነው........

"በመሃል ምድር ቢናወጥ፣ ሰማይ ቢደረመስ ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ እምርታ የምንቀሰቅስበትና ይህንን ህያው አድርገን የምንቀጥልበት "መፈክርም" ሆነ አላማ አምጡ ስንባል ግራ እንጋባለን። ህዝብ በሚልዮን ተራብ ብለን ሰልፍ አንወጣም። ሰራተኛው በአጓጉል ሙሰኛና አድላዊ "የነፃ ገበያ" ተብየ ኢኮኖሚ ጉረሮው ተዘጋ ብለን ሰልፍ አንወጣም ፤ ሃገራችን የባእዳን ሽቀጥ ማራገፊያ ያደረጋት አሰራር ነጋዴውንና የሃገሪቱን አምራች ለኪሳር ሲዳርግና የሰርቶ አደሩ ጉረሮ ሲዘጋ አይተን እንዳላየን እናልፋለን፤ ድህነት እየከፋ ሲመጣ፤ ስራ አጥነት እየተስፋፋ ሲሄድ፣ ካለፉት ስርአታት የወረስናቸውን ማህበራዊ ችግሮች ሳንወጣ በነሱ ላይ አዳዲስ ማህበራዊ ችግሮች ሲደራረቡብንና ሃገራችን በአለም የ ሚታዩ ቀውሶች ሁሉ ቋት ሆና የዋይታና የሰቆቃ ምድር ስትሆን ለነዚህ ችግሮች የምናቀርበው አማራጭ መፍትሄ የለን ም። በአጭሩ ከአስር አመታት ወዲህ እየተባባሱና እየከፉ ለመጡት ችግሮች ገፈት ቀማሽ ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በደፈናው ዴሞክራሲ፣ የህግ የበላይነት፣ ነፃ ምርጫ ከሚሉት ነገሮች አልፈን ለገበሬው ወገኖችን "ለርሃብና ለአስከፊ ድህነት የዳረገህ የወያኔ ፖሊሲ ይኸ ነው፣ እኛ ደግሞ ይህንን አማራጭ ፖሊሲ እናራምዳለን!" ለሰራቸኛው " የችግር ህ መንስኤ ይህ የወያኔ ፖሊሲ ነው፣ እኛ ደግሞ ይህንን እናቀርብልሃለን!" ለነጋዴው፣ ለአሰሪው፣ ለአምራቹ እንደዚሁ ' 'የኛ ይኸ ነው የወያኔ ይኸ ነው!" በሚል የምናቀርበው ምንም አማራጭ የለንም።" በማለት የህዝባችን ትግል መጀመ ሪያውኑ በቅጡ እንዲቀሰቀስና ከዚያም ፍሬ እንዲሰጥ ከተፈለገ በስትራቴጂያዊ ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆን በእነዚህ የኑሮና የህልውና ችግሮችም ላይ ማተኮር እንደሚገባው አስምሮበት ነበር። መኢሶን በዚህ ሰነዱ "ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ እነዚህን አማራጮች አቅርቦ መታገል አስቸጋሪ ስለሆነ መጀመሪያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ታግለን ከዚያ በኋላ ከድል ባሻገር እነዚህን አማራጮች ለህዝብ እናቀርባለን" ለሚሉ በርካታ ወገኖች ይህ አካሄድ ያዘለውን ከባድ ቅራኔ ሲጠቁም ፤

"ያለንበት አጥፊ አዙሪት ግልፅ ነው። ዛሬ ህዝባችንን ወጥረው ከያዙት የህልውና ችግሮች አንፃር 'ቁሱም ዝ ም፣ መፅሃፉም ዝም' የተባለው ሁኔታ ውስጥ ነን። መፍትሄዎቹ ዴሞክራሲ ሲሰፍን ተብሎ ቀን ቀጠሮ ተይዞላቸዋል። እዚህ ላይ ችግሩ ግልፅ ነው። ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የሚደረገው ትግል ግቡ የሚደርሰው ተቃዋሚ ሃይሎች በትጥቅ፣ በገንዘብ፣ በድርጅት አቅምና በዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ከነሱ ልቆ ከሚገኘው ወያኔ ይልቅ የተሻለና ተጨባጭ አማራጭ

ይዘው ህዝባችንን በደርዘን ሚልዮን እያስቆጠሩ ከጎናቸው ሲያሰልፉ ብቻ ነው። ይህንን አማራጭ ካላቀረቡ ህዝቡን ማንቀሳቀስ ስለማይችሉ መጀመሪያውኑ ዴሞክራሲ የሚሰፍንበት ሁኔታ የለም። አማራጭ ለማቅረብ ደግሞ ዴሞክራሲን የሚጠብቁ ከሆነ እኛም ሃገራችንም አስከፊ አዙሪት (ቪሸስ ሰርክል) ውስጥ መሆናችን ግልፅ ይመስለናል።" በማለት በወቅቱ ስለነበርንበት አስቸጋሪ ሁኔታ ያለንን አስተያየት ሰጥተን ነበር።

በግንቦት 97 ምርጫ ዘመቻ ውስጥ እንሳተፍ ያልንበትም አንዱ ምክንያት በዘመቻው ተጠቅመን ለሃገራችን ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ በምንላቸው አማራጮች ዙሪያ ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ እንደነበረ በወቅቱ በሰፊው አብራርተናል።' ህዝባችን በነዚህ አማራጮቹ ዙሪያ በገፍ ከተሳተፈ ደግሞ የኢህአዴግ መሪዎች "አሸንፍን" ለማለት በገፍና "በኢንደስትሪ ደረጃ" አጭበርብረውና በህዝባችንም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲው ፊት ለመጋለጥ መርጠው ስለሚሆን ያኔ ደግሞ በህዝብ ፊት ያጋለጥናቸውና የታገልናቸው የነዚህ የጥፋት ሃይሎች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የህዝባችንን ችግሮች ከመፍታት ይልቅ እንደሚያባብሷቸው ሳይታለም የተፈታ ስለሆነ ትክክለኛነታቸው ከቀን ቀን እየጎላ የሚሄደውን አማራጮቻችንን አንግበን ትግሉን ማፋፋም ይጠበቅብናል ብለን ነበር።

በእኛ ግምት በግንቦት ምርጫ ሳቢያ ይህ የነበርንበት አዙሪት ተሰብሮ ዛሬ የግድ ዘርፈ ብዙ ለሚሆነው ለቀጣዩ ትግል እጅግ ያመቸ መንደርደሪያ ጨብጠናል እንላለን። የግንቦትን ምርጫ በህዝባችን የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ ልዩ ቦታ ከሚሰጡት ምክንያቶች አንዱ የሃገራችን ዴሞክራቶች አማራጭ ፕሮግራማቸውን አንግበው፣ ከኢህአዴግ መሪዎች ጋር በሚልዮኖች ፊት መሟገትን የጨመረ ሰፊ ዘመቻ አካሂደው እነዚህን አማራጮች ለህዝባችን ለማስጨበጥ የበቁበት ሂደት መሆኑ ነው። ህዝባዊ የትግል ማእበል ለመቀስቀስ አንስራ ስንል እኛም ህዝባችንም ጠንቅቀን መረዳት የሚያስፈልገን በግንቦት ቅልበሳ ሳቢያ ከህዝብ ድምፅ ዝርፊያ ጋር ቀርበው የነበሩትና በህዝብ ድምፅ ፀድቀው የነበሩት እነዚህ በጎ የማህበራዊና የኢኮኖሚ አማራጮችም በመዘረፋቸው ምክንያት ህዝባችን በየመስኩ ከቅድመ ግንቦት ከነበረው ሁኔታ ለባሰ የኑሮ ሰቆቃ የተዳረገ መሆኑን ነው። በመሆኑም "ለግንቦት ድሎች" ተብሎ የሚካሄደው ተጋድሎ በእርግጥ "ህዝባዊ" እንዲሆን ከፈለግን በቅልበሳው ምክንያት እየተባባሰ ያለውን የኑሮ መመሰቃቀል በመቃወም ከህዝባችን ጋር መሰለፍ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ዛሬ እንደምናየው ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ለዚህ አመቺ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከመቸውም ጊዜ ይልቅ አስፈላጊ እየሆነ እያየነው ከህዝባችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች አኳያ የሚደረግ ትግል የለም። ተቃዋሚ ድርጅቶች ግንቦት 97 አቅርበዋቸው የነበሩት አማራጮች "የክት ቀን" ልብሰ ይመስል ለቀጣዩ 2002 ወይም ደግሞ ገና ዘንቦ ተባርቆ "ነፃ ምርጫ ለሚቻልበት ወቅት" ተብሎ በይደር የተቀመጡ ይመስላል። የከርሞ ጥጃ በሚመስል አካሄድ ወደ ቅድመ ግንቦቱ አዙሪት በመመለስ ለስትራቴጂያዊ አላማዎችና ለራእዮች ቅድሚያ እየተሰጠ "መጀመሪያ በዴሞክራሲውና በነፃ ምርጫ ትግል " እየተባለ ያለ የሌለ ትኩረትን በፖለቲካው መስክ ላይ የመጣል አዝማሚያ ይታያል። ለመብት የሚደረገው ትግል አያስፈልግም ማለት አይደለም። ለማለት የምንፈልገው የህዝባችንን ኑሮ እያመሰቃቀሉ በሜድ ላይ ያሉትን ቀውሶች እንደ ቅልበሳው መዘዞች አድርገን የሆነ ቀጣይ የምርጫ ዘመቻ ሳንጠብቅ እንንቀሳቀስባቸው ለማለት ነው። ስራ አጡ ለስራ፣ ተፈናቃዩ ገበሬ ማሳውን ማሳውን መልሶ እጁ እንዲያስገባ፣ የዋጋ መናር በኑሮ ጠርዝ ላይ ያንጠለጠለው ወዛደር ለደመወዝ ጭማሪና ለተሻለ የስራ ሁኔታ፣ በተቃዋሚነት ተፈርጆ ከስራው የተፈናቀለ የመንግስት ሰራተኛ ወደ ስራው እንዲመለስ፣ በአድልኦ ፖለቲካ ወይም እንደዚሁ በተቃዋሚነት ተፈርጆ የንግድ እንቅስቃሴውን ለማቋረጥ የተገደደው ነጋዴ ወይም ኢንቬስተር አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ስራውን ቀጥሎ ራሱንም ሃገሩንም እንዲጠቅም.......ከነዚህና ሌሎች ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ከቀውሱ ለመውጣት ያሉትን ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አማራጮች አንግቦና ከነዚህም በተጓዳኝ ደግሞ ዘላቂና ፖለቲካዊ መፍትሄዎችን እየጠቆሙ መንቀሳቀስና ህዝባችንን ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ይህ ትግል አስቸጋሪ ነው ለሚሉ ወገኖች አወን አስቸጋሪ ነው የኢትዮጵያችን የነፃነት ተጋድሎ የአልጋ ባልጋ ጉዞ ሆኖም አያውቅ፣ አይደለም አይሆንምም እንላቸዋለን። እንዲያውም የትግል ስትራቴጂያችንን ለመንደፍ ስንነሳ መንደርደሪያ አድርገን የምንወስደው ይህንን መራራ ሃቅ አስቀድመን በመቀበል መሆን ይኖርበታል። ከዚያ አልፈው ግን በ

ዚህ ሁኔታ እንዲህ አይነቱ ህዝባዊ ትግል "አይቻልም" ለማለት ለሚቃጣቸው ሃይሎች ያለን አጭር መልስ የሃገር ህልውና፣ ሰላም፣ አንድነትና ብልፅግና ጉዳይ ስለሆነ "መቻል አለበት" ብለን ሳለው ሽብርተኛ አገዛዝ የሚመጥን የጋራ ትግል ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልገናል የሚል ነው። "መቻል አለበት" ብለን ከተነሳን ደግሞ በአድርባይነትም ሆነ በትግሉ ከባድነት ተሸንፈው ህዝባችንን ይዞ መታገል አይቻልም የሚለውን ተንበርካኪ እምነታቸውን ለመሸፋፈን ሲሉ ብቻ ይህ አይነቱ ትግል ትርምስና መበጣበጥ ስለሚያመጣ "አላስፈላጊ ነው" የሃገራችንን ችግሮች በብሄራዊ እርቅ መንፈስ በሚካሄድ የሰከነ ድርድር እንፈታቸዋለን ብለው የሚግደረደሩ ሃይሎችን ሃይሎችን ለትግላችን ጥራት፣ አንድነትና ጥንካሬ ስንል በዚህ አቋማቸው በጋራና በቁርጠኝነት ልንታገላቸው ይገባናል። ይህ ማለት ግን "በብሄራዊ እርቅ መንፈስ የሚካሄድን ድርድር" መቃወም እንዳይደለ ግልፅ መሆን አለበት።

መኢሶን የሃገራችን ውስብስብ ችግሮች በአሸናፊና ተሸናፊ ሂደት "እየተፈቱ" የኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባው እስኪላጥ ድረስ ለዘመናት የተንገላታበት የጥፋት አዙሪት እንዲሰበርና በሃገራችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን "የእርቀ ሰላም" ፅንሰ ሃሳብን አንስቶ ከፓሪስ አንድ ጉባኤ ጀምሮ ለብሃራዊ እርቅ ፖለቲካ ሳይታክት የታገለ ድርጅት ነው። በመሆኑም ችግሮችና ግጭቶች በብሄራዊ እርቅ መንፈስ በሚካሄዱ ድርድሮች ይፈቱ በሚለው ሃሳብ ምንም ተቃውሞ የለውም።

የብሄራዊ እርቅ ጥሪ ህብረተሰባችን ለዘመናት ሲኳትንበት ከቆየው የጥፋት አዙሪት ለማውጣትና ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር ያለንን ፅኑ አላማ እውን ለማድረግ ለወያኔ/ኢህአዴግ ደጋፊዎችና አባላት ድል አድራጊው ህዝባችን የሚዘረጋላቸው የእርቅ እጅ (እፊር) እንጂ ጥቂት 'ሃላፊነት የሚሰማቸው' የፖለቲካ መሪዎች ከጥቂት ፀረ ህዝቦች ጋር 'ለመታረቅ' የሚያቀርቡት ጥያቄ ወይም ማመልከቻ አይደለም። እሱም እንደ ነፃ ምርጫ ከዴሞክራሲ መስፈን ውጭ ሊታሰብ የሚችል ነገር አይደለም። ተአማኒነትና ተጨባጭነት የሚኖረው ለአሸባሪዎቹ "እንታረቅ" በሚል መንፈስ በልመና መልክ ሲቀርብ ሳይሆን የህዝባችን ዴሞክራሲያዊ ትግል በቅድሚያ ድል አድርጎ ከሽብር አገዛዝ ዘዴያቸው ለማፈግፈግ ለተገደዱት ወገኖች ከእንግዲህ በዴሞክራሲያዊትና በብሄራዊ እርቅ እውንነት በተረጋጋች አገራችን የስልጣን ጉዳይ ለማንም ይሁን ለማን "የሞት ሽረት" ጥያቄ እንዳልሆነ፤ የዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ማየልና ማሸነፍ ሲከሰት ከዚህ ድል ሁሉም በአሸናፊነት እንደሚወጣ ለማስረገጥ ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የተዘረጋ የህብረሰባዊ እርቅ ጥሪ ነው። በመሆኑም ከዴሞክራታይዜሽኑ ትግል ድል ባሻገር እንጂ ከሱ በመለስ "ብሄራዊ እርቅ" ማለት ትርጉም የለሽ ብቻ ሳይሆን ትርጉም ያለው ብሄራዊ እርቅ እውን ሊሆንበት የሚችለውን ህዝባዊ ትግል የሚያዘናጋ አደገኛ አቋም የሚሆነው።

ድርድር በሚሉትም የትግል ስትራቴጂ ከዚህ የተለየ አቋም ሊኖር አይችልም። ድርድርም እንደ ብሄራዊ እርቅ ጥሪ የሃገራችንን ችግሮች በሰላማዊ ዘዴ ለመፍታት መጀመሪያ በትግል ከፀረ ህዝብ አቋማቸው ለማፈግፈግ ለተገደዱት ሃይሎች የነሱንም ህጋዊ ጥቅሞች፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሚያስተናግድ ሁኔታ ከቀውስ የሚወጣበትን ተጨባጭ ዘዴ ለማመቻቸት የሚገባበት ሂደት እንጅ በቅድሚያና በትግል እውን ያልሆነ ዴሞክራሲን በጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይቶ ለማምጣት የምንጠቀምበት ዘዴ ሊሆን አይችልም። ከዚህ ውጭ የህዝባችንን ትግል ሊተካ በሚግደረደር የድርድር ጎዳና ለመሰማራት መሞከር በቀጥታ በኢህአዴግ መሪዎች ወጥመድ ውስጥ ገብቶ መዳከር እንደሆነ በመስከረም ወር 1998 እ.ም. እነ መለስ ዜናዊ የህዝባችን ትግል አይሎና ብርክ አስይዙዋቸው የሶስት ቀን የቤት መዋሉን አድማ ለማክሸፍ በድርድር ስም የጠነሰሱትንና የተሳካላቸውን ሴራ ዘወር ብሎ ማየት ብቻ ይበቃል። ከዚህ መራራ ልምዳችን በመነሳት ዛሬ እኛ ዋናው የጊዜው ተግባር የህዝባችንን የትግል ማእበል መልሶ መቀስቀስና መልሶ ወደ አጥቂነት ማሸጋገር ነው ብለን የምንነሳ ሃይሎች በዚህ መልክ "ድርድር" "ብሄራዊ እርቅ" "አለም አቀፉ ኮሙኒቲ" እየተባለ ለሚቀርብልን ትጥቅ አስፈቺ ጥሪ የምንሰጠውና መስጠት የምንችለው አጭርና ግልፅ መልስ "አድርሰናል" የሚል መሆን ይኖርበታል።

እንግዲህ የሚልዮኖች የትግል ውጤት የሆኑትን ግንቦትን ድሎች ለማስመለስ የሚልዮኖች ትግል ያስፈልጋል በሚለው ስምምነት ካለ ከዚህ የሚቀጥለው ጥያቄ እነዚህ ሚልዮኖች በማን አንቀሳቃሽነትና እንዴት ይንቀሳቀሱ? የሚለው ጥያቄ ይነሳል። ለህዝባዊ አጀንዳ በህዝባዊ ትግል ካልን በኋላ ለዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው "ህዝባዊ አመራር" ያልነው መፈክር ለዚህ ወሳኝ ጥያቄ የመልስ ሃሳብ ለመሰንዘር ነው።

## 3/ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ አመራር

ዛሬ የተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህዝብ ፊት ተወዳድረው ስልጣን ለመጨበጥ የሚያካሂዱት የምርጫ ዘመቻ የፖለቲካ ትግል ወይም ደግሞ የኢህአዴግን መንግስት አስወግዶ በሌላ ሃይል በመተካት የሚወሰን ትግል አይደለም። በዚህ ጉዳይ ከስድስት አመታት በፊት መኢሶን ''ተሸጋጋሪው ማነው? አሸጋጋሪውስ?'' በሚል ርእስ ባሰራጨው ጥናታዊ ሰነድ ይህ የጊዜው አንገብጋቢ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉዳይ ከፖለቲካ ድርጅቶችም ፤ ከምርጫ ሰሞን ግርግርም፤ ከመንግስት ስልጣን ቅብብሎሽ ሂደትም አልፎ የሚሄድ ሰፊ አገራዊ አጀንዳ እንደሆነ ሲጠቁም

''...... ከለንደኦም ጉባኤ ጉድለቶችም ሆነ ከሃገራችን 'የሽግግሮች' ታሪክ መቅሰም ያለብን ትምህርት ሽግግር በአመፅ፤ ጊዜያዊ የበላይነትን ያገኘው ወገን የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ህብረተሰቡን እስከ ወዲያኛው 'አሸነፍኩ' በሚልበት ፍጥጫ፤ በአሸናፊና ተሸናፊ መሃከል ወይም ደግሞ በባእዳን አቀነባባሪነትና አስተናጋጅነት 'አሉ' በሚባሉ ጥቂት የፖለቲካ ሃይሎች መሃከል በዝግ ችሎት የሚደረግ የስልጣን ቅብብሎሽ ላይ ማተኮር የለበትም የሚል ትምህርት ነው። ከዚህ ይልቅ ሽግግሩ እስከ ተቻለ ድረስ በስምምነት፤ በ'ኮምፕሮማይዝ' እንዲከናወን፤ ህብረተሰባችንም በዚህ የሽግግር ወቅት በእያንዳንዷ ቀን ይበልጥ ዴሞክራቲክና ይበልጥ የተረጋጋ መልክ እየያዘ፤ ህዝባችንም በእያንዳንዷ ቀን ይበልጥ ንቁ ተሳትፎ እያደረገና ይበልጥ እየተደራጀ፤ ለመጭው የተሻለ ስርአት ይበልጥ ራሱን እያመቻቸ የሚሄድበት የታሪክ ወቅት እንዲሆን መታገል ያስፈልጋል ማለት ነው።'' ካለ በኋላ ድርጅታችን በዚሁ ሰነድ ላይ ሃገራችን የሚያስፈልጋት ''የህብረተሰብ ሽግግር'' እንደሆነ በግልፅ አስረግጦ እንደዚህ አይነቱ ሽግግር የማን ሃላፊነትና በማን ላይ የተጣለ አደራ እንደሚሆን በጠቆመበት ክፍል፤

''ተሸጋጋሪው ህብረተሰባችን እንደአለ እንደ መሆኑ መጠን አሸጋጋሪውም ራሱ ህብረተሰቡ መሆን ይገባዋል እንላለን። ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ.....የዚህ የሽግግር ሃላፊነት ለማንም ይሁን ለማን 'ሃገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አሸጋግራለሁ' ብሎ ቃል ለሚገባ ጊዜያዊ ይባል የሽግግር፤ ጥምር ይሁን አንድ 'ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ግንባር' ለሚመራው መንግስት የሚተው ጉዳይ መሆን የለበትም። ይህ ሃላፊነት እንደ ደቡብ አፍሪካው የሽግግር ሂደት ከማንኛውም መንግስት ውጭ ሆኖ ለሚሰራ፤ በአጠቃላይ የሃገሪቱን የዴሞክራታይዜሽን ሂደት ከማንም የፖለቲካ ሆነ ሌላ ሃይል ወገናዊ ቁጥጥር ውጭ በበላይነት ለሚያቅድና ለሚያስፈፅም አካል መተው ይኖርበታል።'' በማለት ሰፊና አገራዊ የሆነ ራእዩን አስቀምጧል።

ሰነዳችን በዚህ የሽግግር ወቅት ሃገሪቱን የሚያስተዳድር መንግስታዊ መዋቅርም አስፈላጊነቱ የማያጠራጥር በመሆኑ ስለሚቋቋመው አስተዳደር (ኬር ቴከር ገቨርንሜንት) ያለውን አማራጭ ሲያቀርብ የኢህአዴግ መሪዎች በህዝብ ትግል ከተወገዱ በኋላ ''በሽግግሩ ሂደት እጁን የማያስገባና ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥያቄዎች ምንም አይነት ዘላቂነት ያላቸው ውሳኔዎች የማድረግ ስልጣን የሌለው ጊዜያዊ አስተዳደር መሰየም'' አስፈላጊ እንደሚሆን ጠቁሟል።

ኢዴሃህም ለግንቦት 97 ምርጫ ባወጣው አማራጭ ሰነድ ሃገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ህብረተሰብ የማሸጋገሩን ጉዳይ በሚገባ በማጤን በፕሮግራሙ ሁለተኛ ክፍል ለዚህ ሽግግር አስፈላጊ ያላቸውን ሁለት አካላት ማለትም የዴሞክራሲያዊ ሂደት የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽኖች ስለሚሰየሙበት ሁኔታና ስለሚጠብቃቸው ተግባር በሰፊው አስቀምጧል። ከዚህም በመነሳት የሚባል አንድ ቁምነገር ቢኖር የዛሬው የኛ የዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ስትራቴጂያዊ አላማ የኢህአዴግ መንግስት በህዝብ ትግል እንዲያፈገፍግ ወይም ደግሞ እንዲወገድ ተደርጎ ለተያዘው ህዝባዊ ተጋድሎ ወሳኝ የሚሆነው ''የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ'' እውን እንዲሆንና በዚህ ጉባኤ በሚሰየሙት ሁለቱ ኮሚሽኖች አማካኝነት ዴሞክራሲ ጎልብቶ፣ ብሄራዊ እርቅ ወርዶ አጠቃላዩን ሂደት በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ብሎም በነፃ ምርጫ ለመቋጠር መታገል ይሆናል ማለት ነው።

እንደዚህ አይነቱ የሽግግር ጉባኤ ተሳታፊዎቹ እነማን እንደሆኑና ተግባራቱስ ምን እንደሚሆኑ በኢዴሃህ መግለጫዎች በተደጋጋሚ የተጠቆሙ ስለሆኑ አንባቢ ከነዚህ መሃከል በህብረቱ አማራጭ ሰነድ ክፍል ሁለት ውስጥ የተዘረዘሩትን ነጥቦች እንዲመለከት እየጋበዝን ለጊዜው እዚህ ወሳኝና ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለመድረስ የሚደረገው የግድ ዘርፈ ብዙ የሆነ ህዝባዊ ትግል ስለሚያስፈልገው አመራር ተግባራትና ይህ አይነቱ አመራር እውንና ፍሬያማ እንዲሆን መሟላት ስለሚኖርባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ያለንን ሃሳብ ለማቅረብ እንሞክራለን።

ከፍ ብለን ካወሳናቸው በርካታ የትግል መስኮች አንፃር ሲታይ የእንዲህ አይነቱ አመራር ተግባራት ሰፋፊና ውስብስብ እንደሚሆኑ የታወቀ ነው። እንዲህ አይነቱ አመራር ከፍ ብለን እንዳልነው ሁሉም ብሶቱን አንግቦ እንዲነሳ ጥሪ ከማድረግ አልፎ መሄድና እንደ የካቲት ማለዳ ወቅት ሁሉም "ብሶትህ ብሶቴ" በሚልና "በእርዳ ተራዳ" መንፈስ በአንድ ላይ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ሃላፊነት ይጠበቅበታል። እንደዚህ አይነቱ ህዝባዊ አመራር በዚህ መልክ የሚንቀሳቀሱት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዛሬ የሚገኙበት ከባድ ቀውስ የግንቦት አማራጮች ዝርፊያ ወጤት እንደሆነ ተገንዝበው ማንኛውም ዘላቂነት ያለው መፍትሄ የኢህአዴግ መንግስት ከስልጣን መወገድና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ከህዝብ ድምፅ የፈለቀና በህዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግስት እንደሆነ አውቀው ለዴሞክራሲ እንዲታገሉ የመቀስቀስና ግንቦት ላይ በነበረው የአንድነት፣ የወንድማማችነትና የትግግዝ መንፈስ የሚካሄድ ትግላቸውንም የማስተባበር ሃላፊነት የሚቀበል አመራር መሆን ይኖርበታል። በእንደዚህ አይነቱ የግድ ሁሉን አቀፍ መሆን የሚኖርበት አመራር አማካኝነት ህዝባችን በድል አድራጊነት እንዲወጣ ከተፈለገ ደግሞ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች በቅድሚያ ሊታሰብባቸውና ሊሟሉ ይገባል እንላለን።

አንደኛ መጀመሪያውኑ ህዝባችንን ተነስ ታገል ብለን ስንጠራው ይህ ጥሪያችን ተደማጭነት እንዲያገኝ ከፈለግን በቅድሚያ ተአማኒነትን መልሰን መገንባት ይኖርብናል። ሁለተኛ ደግሞ ይህ ተአማኒነት ያለው አመራር ትግሉን ከቀሰቀሰ በኋላ እንዳለፈው ጊዜ በኢህአዴግ የመጀመሪያ "የመልስ ምት" ተፍረክርኮ ታጋይ ህዝባችን እንደገና ለአደጋ እንዳይዳረግ ከማይቀረው የአፈና ውርጅብኝ ባሻገር ቀጣይነቱ የሚረጋገጥበት ዘዴ ከወዲሁ መመቻቸት ይኖርበታል።

ተአማኒነትን መልሶ መገንባት ስንል ምን ለማለት ነው? ግንባር ቀደም ሃይሎች በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ዛሬ በሰፈነው ጨለምተኝነትና ራሳቸው በፈፀሟቸው ስህተቶች የተነሳ በቅድመ ግንቦቱና በግንቦት አፍላ ወቅት በህብረተሰቡ የነበራቸው ተአማኒነት እንደሌለ ጠንቅቀው መገንዘብ አለባቸው። ትግላችንን ለዚህ ያበቁት እዚህ ተዘርዝረው የማያልቁ በርካታ ምክንያቶች ናቸው። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል።

መጀመሪያ በግንቦት ማግስት ህዝባችን በግብታዊነት ሰላማዊ ሰልፎች፣ የስራ ማቆም አድማዎች ወዘተ እያደረገ ሲሰዋ በነበረበት ወቅት ለዚህ ትግል የተቀነባበረ አመራር የሚሰጥ ሃይል ጠፍቶ ሁሉም ተራ በተራ እየተነሳ የተሰዋበት ሁኔታ ተከስቷል። ተማሪውና ወጣቱ አንዴ ደሴ፣ አንዴ ድሬዳዋ፣ አንዴ ጎንደር፣ አንዴ አዋሳ፣ አንዴ ጅማ አንዴ አዲስ አበባ ሲንቀሳቀስና ሲሰዋ ወጣቱና ተማሪው በያለበት በአንድ ቀን እንዲነሳ የሚጠራና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል መሪና አቀናባሪ ሃይል ብቅ አላለም። በሃገር ደረጃ ቀርቶ በአዲስ አበባ እንኳን የአመራር ክፍተት ስለነበረ የተለያዩ ት/ቤቶች በተለያዩ ቀናት እየተነሱ ወጣቱ ተራ በተራ ሲሰዋ ተመልክተናል። የወጣቱ የተቀነባበረ አነሳስ ለተያዘው ትግል ምን ያህል ስንልቡናዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ እምርታ ሊሰጥ ይችል እንደነበረ እየታወቀ ይህ ሊደረግ አልቻለም። በዚህ ላይ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች ነን ባዮች የፈረንጆቹን ጥሪ እየቀለቡ በተፋፋመ የትግል ወቅት "ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል" እንደተባለው "መንግስትም ተቃዋሚውም ወገን ነገሮችን በእርጋታና በጥሞና እንዲይዙ" የሚል ይፋ ጥሪ እስከማስተጋባት መሄዳቸው ትግሉን አስተባብሮ ለመምራት ስላሳቸው ብቃት ህዝቡ ራሱን እንዲጠይቅ እንዳደረገው ግልፅ ነው።።

ሁለተኛ በነዚሁ ቁልፍ በሆኑ የግንቦት ማግስት ወራት ህዝቡ ለመታገልና ለመሰዋት ይህ ነው የማይባል ወኔ እያሳየ ሳለ ግንባር ቀደም ነን የሚሉ ሃይሎች አመራር እንሰጣለን ብለው በተግደረደሩባቸው አንዳንድ አጋጣሚዎች እንኳን ለህዝቡ የትግል ወኔ የሚመጥን ቆራጥነትና ፅናት አለማሳየታቸው ህብረተሰቡ አመኔታ እንዲያጣ እንዳደረገው ግልፅ ይመስለናል። እነዚህ ወገኖች በዚያ ቀውጢ ጊዜ አንዴ ሰልፍ ውጣ ብለው ጥሪ አድርገው በማግስቱ ሰልፉ ተሰርዟል ሲሉት፣ አንዴ የሙት ከተማ አድማ ቀትር ላይ አውጀው ኢህአዴግ ብርክ ሲይዘውና ህዝባችን ደግሞ በአጥቂነት መንፈ

ሱ ተመቻችቶ ለአድማው ሲዘጋጅ ማታ በቴሌቪዥን ቀርበው ''ተሰርዟል'' ብለው ሲያረዱት፣ አንዴ ለአገር አቀፍ የተ
ወዳዳሪዎች ጉባኤ አዲስ አበባ ክተቱ ተብለው ሰባት መቶ የሚጠጉ ዜጎች ከመላ ሃገሪቱ ይህንን የትግል ጥሪ አክብረው
አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ ሌላው ቢቀር በወቅቱ አንዳንድ ዜጎች እንደወተወቱት ድንኳን ጥሎ መሰብሰብ ሲቻል ''የስ
ብሰባ አዳራሽ ጠፋ'' ተብሎ ይህ ታሪካዊና ለትግሉ አዲስና አገር አቀፍ እምርታ ሊሰጥ ይችል የነበረ ጉባኤ ተሰርዞ ታጋ
ዩ ሁሉ አንገቱን ደፍቶ ወደ የመጣበት ሲመለስ ታዝበናል። የዚህ ሁሉ ''የመመሪያዎች ዥዋዥዌ'' ውጤት የትጥቅ ትግ
ል መፍታቱን ሂደት ማገዝ ብቻ ሳይሆን ይህንን ትግል እመራለሁ ባዮችም በህዝብ ፊት ተአማኒነት እንዲያጡ እንዳደ
ረጋቸው የሚያጠራጥር አይደለም።

ሶስተኛው የተአማኒነት መጥፋት ምክንያት ስለ ትግል አንድነት በሚለፈፈውና በተጨባጭ በሚታየው ሃቅ መሃ
ከል ያለው ቅራኔ ሆኖ እናገኘዋለን። ግንባር ቀደም መሪዎች ነን የሚሉ ሃይሎች እዛው በዛው ህዝባችንን ለትግል አንድ
ነት እየጠሩ እነሱ ራሳቸው ግን ሲከፋፈሉና ሲቦጫጨቁ ይታያሉ። ዛሬ የፖለቲካ መሪ ነኝ ብሎ በየስብሰባው፣ በየሴሚ
ናሩ፣ በየመድረኩና በየጉባኤው ስለ ''ጋራ ትግል አስፈላጊነት'' የማይለፍፍ መሪ ወይም ታጋይ የለም። ደግሞ ተደጋግሞ
ህዝባችን ''እንደ አንድ ሰው ሆኖ እንዲነሳ'' የሚደረጉ ጥሪዎች እስካሁን ምንም አዳማጭ ያላገኙበት ምክንያት ጥሪ
አድራጊዎቹ በአርአያነት አለመቆማቸው ብቻ ሳይሆን ከነዚህ መሪዎች አንዳንዶቹ ''በአንድነት ተነስ'' የሚለውን ጥሪ ''
ከኔ ስር ሆነህ!'' ከሚለው ወገናዊና ጠባብ ጥሪ ጋር በተጓዳኝ ሲያስተጋቡ መታየታቸው ሆኖ እናገኘዋለን።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ተአማኒነት ያለው አመራር ልንገነባ የምንችለው ካለፉት ስህተቶች ተምረን ለዚህ ዘርፈ ብ
ዙ ተጋድሎ ከፖለቲካ ድርጅቶች-፣ ከሲቪክ ማህበራት ተወካዮች፣ ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከታዋቂ አገር ወዳድ ግለሰቦ
ች፣ ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች፣ ከምሁራን ወዘተ የተውጣጣ የጋራ አመራር ፈጥረን በአንድነት ተነስ ለምንለው ህዝብ በ
አርአያነት የምናሳየው ሁሉን አቀፍ የሆነ አመራር መገንባት የምንችልበትን ዘዴ ተወያይተን ስንቀይስ ብቻ ነው። ለዚያ
ውም ደግሞ እንዲህ አይነቱን አመራር የመገንባቱ ጉዳይ ለትግላችን ወሳኝ ምእራፍ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ ግልፅ መሆ
ን ይኖርበታል። ተአማኒነት ያለው አመራር ፈጥረን ህዝባችን ለትግል መልሶ ቢነሳሳ ይህ አመራር የትግሉን ቀጣይነት የ
ሚያረጋግጥበት ሁኔታ ከወዲሁ ማመቻቸት ይኖርበታል።

ቀጣይነት ያለው አመራር ስንል ምን ለማለት ነው? የትግሉን ቀጣይነት እናረጋግጥ ስንል እዚህም ላይ ካለፈው
ሂደታችን ከቀሰምነውና ህዝባችን ከባድ መስዋእትነት እንዲገብር ካደረጉት ስህተቶች አስፈላጊውን ትምህርት በመቅሰ
ም ነው። በዚህ የአመራር ቀጣይነት ጉዳይ መኢሶን ራሱ ከባድ መስዋእትነት የከፈለበት መራራ የሆነ ትምህርት አለው
። በአብዮቱ ወቅት ህዝባችንን ማንቃትና ማደራጀት ለሚል የተቀደሰና ትክክለኛ አላማ ሲል ያለ የሌለ ሃይሉን በህጋዊ
ው የትግል መድረክ በይፋ ሲያሰማራ ''ችግር ቢደርስስ?' የምትለዋን ጥያቄ ቢያነሳም ለቀጣዩ የትግል ምእራፍ የህቡእ
መዋቅሩን ሁኔታው በሚጠይቀው መልክና ፍጥነት አላደራጀም ነበር። በዚህና በመሳሰሉ ሌሎች ስህተቶች የተከፈለውን
መከራ የምናውቀው ስለሆነ እዚህ ላይ አንዘረዝራቸውም። ዛሬም በግንቦት ማግስት የደረሰውና በመድረስ ላይ ያለው
ችግር ከዚህ የተለየ አይደለም።

ግንቦትን በቀደሙት ወራት እነ አቶ መለስ ''እንከን የለሽ ምርጫ እናካሂዳለን'' ሲሉ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች
መሪዎች ከነሱ ጋር ''እኩል ቤት ገብተው'' በሚልዮኖች ፊት ከዚህ በፊት ባልታየ ሁኔታ ሲከራከሩ፣ አንዲት ጥይት ሳ
ትተኮስበት ከሁለት ሚልዮን ህዝብ በላይ አደባባይ ሰልፍ ወጥቶ ለተቃዋሚዎች ድጋፍ መስጠት ሲችል፣ ይህንን ሁሉ
ሂደት ለመታዘብ አሁንም ከዚህ በፊት ባልታየ ብዛት አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ታዛቢዎቹን ማሰማራቱ.....ይህ ሁሉ ለትግሉ
ከወዲሁ ዴሞክራሲ በሰፈነባት አገር የሚካሄድ ''ስልጡን'' ገፅታ ሰጥቶት እንደነበረ ግልፅ ይመስለናል። ይህ ወቅት ለ
ኛም፣ ለኢትዮጵያ ህዝብም፣ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲም ሃገራችን ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብ የበሰሉና የረቀቁ የ
ፖለቲካ መሪዎች እንዳሏት ያሳየ እንደነበረ መጠራጠር አይቻልም። በዚያው ልክ ደግሞ በቀጠሉት ወራት የትግሉ እው
ነተኛ ይዘት ገና ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ከአንድ ፀረ ህዝብና አፋኝ አገዛዝ ጋር በሚካሄድ ገፅታው አፍጦ አግጦ
ሲታይ ያለው የፖለቲካ አመራር ከሽብርተኛው ኢህአዴግ ጋር ለሚደረገው ቀጣይ፣ ውስብስብና እልህ አስጨራሽ ሊሆ
ን የሚችል ትግል በቂ ዝግጅት እንዳልነበረው የታየ መሆኑን መካድ ለመጭው ጊዜ አስፈላጊውን ትምህርት እንዳንቀስ
ም የሚያዘናጋ አጉል አካሄድ እንደሆነ ግልፅ ይመስለናል።

ትግሉ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ እንዳለን ተቆጥሮ በመካሄዱ ከግንባር ቀደሙ ታጋይ የተወሰነው ክፍል "ችግር ቢመጣ" በሚል የጥንቃቄ አካሄድ ይፋ ከመውጣት ተቆጥቦ ጠንካራ የሆነ የህቡእ መዋቅር እንዳይዘረጋ አድርጓል። ሌላው ቀርቶ ደጋፊው ነጋዴም ሆነ የመንግስት ሰራተኛ ሁሉ የሚያደርገው መዋጮ ደረሰኝ በስሙ እየተመዘገበ በኮምፕዩተር እንዲያዝ የማድረግና የመሳሰሉ አይን ያወጡ ስህተቶች ተፈፅመዋል። ይህ ራሱ በርካታ ዜጎችን ለአስከፊ አፈና ያጋለጠ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ "ለክፉ ቀን" ተብሎ የተዘጋጀ ህቡእ አመራር ባለመኖሩ በያለበት የታወቁ የትግሉ መሪዎች ሲገደሉ፣ ሲታሰሩ፣ ሲሰደዱ ትግሉ በዚያው ልክ እንዲዝረከረክና ቀጣይነት እንዲያጣ በመደረጉ ዛሬ ያለንበት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን።

ከዚህ ሁኔታ ለቀጣዩ ትግላችን የምንቀስመው ትምህርት ከፀሃይ በደራ ሁኔታ ግልፅ ይመስለናል። ከፍ ብለን ድሮውንም ተአማኒነት ያለው አመራር ሳንፈጥር ካሁን ወዲያ ለህዝባችን የትግል ጥሪ እናድርግ ብንል እንዲህ አይነቱ ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ሳያገናዝብ የሚደረግና አዳማጭ አጥቶ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ የትጥቅ መፍታቱንና የጨለምተኝነቱን ክስተት የሚያግዝ አደገኛና የአጉል ግንባር ቀደሞች አካሄድ እንደሚሆን ጠቁመናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ ተአማኒነትን ገንብተን ህዝባችን ለትግል ጥሪያችን አወንታዊ መልስ ሰጥቶ መንቀሳቀስ ቢጀምር እንኳን "አደጋ ቢደርስ" አመራሩን የሚተካ ሌላ ህቡእ አመራር ሳይገነባ የትግሉን አመራር ቀጣይነት ሳያበጅ ከእንግዲህ በምስኪን ድርጅታዊ ወይም የአንጃ ስሌት የሚወረወር ማንኛውም ጥሪ ሃላፊነት የጎደለው፣ ካለፈው ምንም ትምህርት ያልቀሰመ፣ አንድ ህዝብ ታግሎ ገኙዎችን ብርክ ካስያዘ በኋላ ቀጣይ ትግል ከሌለ አስከፊ ቀጣይ አፈና እንደሚጠብቀው ያልተገነዘበና ካለፈው አፈና ያላገገመውን ህዝባችንን ለሌላ አስከፊ የአፈና ዙር አጋልጦ የመስጠትን ያህል አደገኛ አካሄድ እንደሆን በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል።

እንግዲህ ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው አመራር አስፈላጊነት በዚህ መልክ ካስቀመጥን ዘንዳ እንዴት እንዲህ አይነቱን አመራር እንፍጠር የሚለው ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። በዚህ በኩል የምንሰጠው አጭር መልስ በግንቦት ህዝባዊ አጀንዳ አንግበው፣ ለዚህ ደግሞ ሚልዮኖችን የሚያንቀሳቅስ ህዝባዊ ትግል ያስፈልጋል ብለው የሚያምኑ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ለጊዜው በውጭ አገር አንድ በቅድሚያ በጥንቃቄና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ የሚዘጋጅ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጠርተው ሰፊ ውይይት የሚያደርጉበት ጉዳይ መሆን አለበት፣ ማንም ድርጅት ወይም ስብስብ በዚህ በኩል ሃሳብ ካለው ለእንዲህ አይነቱ ሸንጎ ሊያቀርበው ይችላል የሚል መልስ ነው።

ይህ በውጭ አገር ይጠራ የምንለው ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ሃሳብ የሚፈልቀው ለጊዜው ባለው ሁኔታ አሰገዳጅነት ብቻ አይደለም። አስፈላጊ የሚያደርጉትም ሌሎች በርካታ ምክንያቶች አሉ። የእንዲህ አይነቱን ጉባኤ ሃሳብ በተነሳ ቁጥር "ዋናው ትግል አገር ቤት ነው" በሚል ሰበብ ተነስተው ለማጣጣልና የዲያስፖራውን ሚና በስንቅ አቀባይነት ብቻ ለመወሰን የሚጥሩ ወገኖች አሉ። ይህ አይነቱ ክርክር ልክ የኢህአዴግ መንግስት በአንድ በኩል በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ተሳትፎ በህገ መንግስቱ አግዶ በሌላ በኩል ደግሞ በኢኮኖሚው መስክ "ኑ ገንዘባችሁን ይዛችሁ ለሃገር እድገት አስተዋፅኦ አድርጉ" እያለ ነጋ ጠባ ከሚሰነዝረው ጥሪ የተለየ አይደለም። የሆነ ሆኖ ግን ይህንን ሃሳብ ለመቃወም የሚቃጣቸው ወገኖች ክርክሩን ባልተባለ አቅጣጫ ለመውሰድ እንደሚጥሩ ግልፅ ነው። የሃገራችን የነፃነት ተጋድሎ ዋናው ሃይልና የትግሉ አምብርት እዛው ሃገራችን ውስጥ እንደሆነ የሚክድ ማንም የለም። የትግላችን ወሳኝ ምእራፍ የምንለው በህዝባዊ ተጋድሎ የኢህአዴግ መሪዎች ተሸንፈው በሃገራችን ምድር የሚሰየመው ሁሉን አቀፍ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። ጥያቄው እዚህ ላይ አይመስለንም።

ጥያቄው በኢኮኖሚ አቅም፣ በእውቀት፣ በፖለቲካ ትግል ልምድ፣ በቁጥሩ በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የዳበረውና ምናልባትም የየትም አገር ዲያስፖራ በማያሳየው መልክ ለእናት አገሩ በመዋደቅ የታወቀው በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ለዚህ እዛው ሃገራችን ምድር ለሚጠራው የዴሞክራሲያዊ የሽግግር ጉባኤ ለሚደረገው ትግል አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጥያቄ ነው። መልሳችን ደግሞ "አወን ይችላል" የሚል መልስ ነው። ይህንን ካልን ደግሞ ሌላ መሰረታዊ ጥያቄ ይነሳል። አስተዋፅኦው የሚያመረቃ ውጤት መስጠት የሚችለው አሁን እንደሚታየው ሁሉም በየበኩል በየፊናውና በተዘበራረቀ መልክ ቢቀጥል ነው ወይስ ገንዘቡን፣ ጉልበቱን፣ እውቀቱን፣ ጊዜውን አስተባብሮና አቀነባብሮ በጋራ በአንድ አቅጣጫ ቢራመድና የሃገር ቤቱ ትግል ጋር በጥንቃቄ ተሳስሮ የሚ

ሰራበት መንገድ ቢበጅ? የሚለው ጥያቄ ይነሳል። ለዚህም መልሱ በጣም ግልፅ ነው። የጋራ ትግሉን ለማስተባበር የጋራ የትግል መድረክ መፍጠሩ የዲያስፖራውን አስተዋፅኦ የሚያጎለብት እንጂ የሚያኮስስ አይሆንም።

በውጭም ቢሆኑ ከወዲሁ በትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የድጋፍ ኮሚቴዎቻቸው፣ የሲቪክ ሰብስ ቦች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የጋዜጠኞች ወዘተ ማህበራት ተወካዮች የምሁራንና የታዋቂ አገር ወዳድ ተወካዮች ተገናኝ ተው "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" ብለው ለጋራ ትግል፣ የጋራ ስትራቴጂና አታጋይ አካል ለመፍጠር ይጣሩ የሚለውን ሃሳ ብ ለመቃወም እስካሁን አንድ እዚህ ግባ የሚባል ምክንያት የሰጠ ዜጋ አላጋጠመንም። ሆኖም

ነገ በሃገራችን ምድር ለማየት በምንፈልገው መድበለ ፓርቲ ስርአት አይነት የተሰበጣጠሩ የፖለቲካም ሆነ ሌ ሎች ሃይሎች ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሰፊ ዴሞክራሲያዊ መድረክ ስለሚሆን በዚያ ውስጥ "እንዋጣለን" ከሚል "ስጋት" ተነስተው ሃሳቡን በቀጥታ የሚያጣጥሉ ወይም ደግሞ የደገፉ መስለው ሳይደግፉ አጀንዳውን የማድበስበስ ስት ራቴጂ የሚከተሉ ሃይሎች እንዳሉ ጠንቅቀን እናውቃለን። ግን በኛ ግምት ከዚህ ይልቅ ያለው ችግር ከፖለቲካ ሃይሎ ችም፣ ከሲቪኩ ማህበረሰብ ተወካዮችም፣ ከታዋቂ ምሁራንና ግለሰቦችም በርካታ ወገኖች እያነሱ የሚጥሉት ይህ የሁ ሉን አቀፍ ጉባኤ ሃሳብ "የሁሉም አጀንዳ" ሆኖ እዚያው በዚያው ደግሞ ባለቤት ያጣ ከመሆኑ የሚፈልቅ ችግር ይመስ ለናል።

በኢዴሃህ በተደጋጋሚ የተጠቀመው አካሄድ የታጋይ ሃይሎች "መሸጋሸግ" የሚል ነውና እንዲህ አይነቱ ጉባኤ "ተቃዋሚ ነኝ" የሚለው ሁሉ እስኪሰባሰብ መጠበቅ ስለማይኖርበት በየድርጅቶች፣ በየድጋፍ ኮሚቴዎች፣ በየሲ ቪክ ማህበራት በዚህ ሃሳብ የሚስማሙ ሃይሎች የየድርጅቶቻቸውን ጠባብ አጥር ሰብረው ከሌሎች በመግጠም ለዚህ አላማ መስራት ይኖርባቸዋል እንላለን። ጊዜ ስቀልባሾቹ እንጂ ለኛ እንደማይሰራና ትግላችን ከአደገኛ ዳተኝነትም ጋር መሆኑን ተገንዝበን በሆነ ባልሆነ ነገር ሊያራዝሙ የሚሞክሩ ሃይሎችን ወደ ጎን ትቶ ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር ይህን ን ጉባኤ ተግባራዊ ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል። "መሸጋሸግ" ከሚለው ሃሳብ ሌላ እዴሃህ የጠቀመው ስትራቴጂ የግ ንቦት ሃይሎች "የመሰባሰብ" ሂደት ነውና በህዝባችን ጎን የፀናን ወገኖች በአንድነት ከቆምን ቁጥራችን አነሰ የሚል ስጋ ት ሊኖረን አይገባም። ተሸጋሽገንና ተሰባስበን እናካሂድ የምንለው ትግል የሃገሩም፣ የትግሉም ባለቤትና የተያዘው ቅልበ ሳ ገፊት ቀማሽ የሆኑትን ሚልዮኖችን በግልፅና ህዝባዊ አማራጭ ዙሪያ የማታገል አላማ እስካነገበ ድረስ የጥራትና የቁ ርጠኝነት እንጂ የቁጥር ችግር እንደሌለ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

## የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)

ግንቦት 2000 ዓ.ም.